# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 100 ታኅሣሥ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ



ፎቶ፡ በረሀኑ ታደሰ

አቶ መሳፍንት ተፈራ



አቶ ጌትነት ታደሰ






# ምክር ቤቱ

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሹመትን አፀደቀ

### - የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ሹመትም ጸድቋል

**ተስፋ ፈሩ**


አዲስ አበባ፡- 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 9ኛ መደበኛ ስብሰባው የወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢነት ሹመት አፅድቋል።

ምክር ቤቱ የአቶ መሳፍንት ተፈራን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚነት እንዲሁም የአቶ ጌትነት ታደሰን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚነት ሹመቶችንም አፅድቋል፡፡

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢነት ሹመትን ለምክር ቤቱ ያቀረቡት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ በሰጡት ማብራሪያ፤ ባለፉት ጊዜያት ከተገነቡ ውጤታማ ተቋማት መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መሆኑን ገልጸው፣ ሥራ በለቀቁት የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ምትክ የቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሆኑ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመጨረሻ ዕጩ ሆነው መቅረባቸውን በመግለጽ ምክር ቤቱ ሹመቱን እንዲያጸድቅ ጠይቀዋል።

የምክር ቤቱ አባላት የመጨረሻ ዕጩ ሆነው በቀረቡት ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ ላይ አስተያየት ከሰጡ በኋላ፣

ምክር ቤቱ ... ወደ ገጽ8 ዞሯል



ዓሊ አብዲ

# በሶማሌ ክልል

## ለሽብር ጥቃት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 14 የአልሸባብ አባላት በቁጥጥር ሥር ዋሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጅግጅጋን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የሽብር ጥቃት ለመፈጸም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 14 የአልሸባብ የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል አስታወቀ፡፡ አልሸባብ የሽብር ጥቃቶችን እንዲፈጽሙ ስምሪት የሰጠው በሶማሌ ክልል

በሶማሌ ክልል ... ወደ ገጽ8 ዞሯል

# በአማራ ክልል ከ300 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ ለማልማት እየተሠራ ነው

### - በመኸር ግብርና ከታረሰው 67 በመቶው ሰብል ተሰብስቧል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በዘንድሮው ዓመት ከ333 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ ለማልማት እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በ2015/16 የመኸር እርሻ ከለማው ከ5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ሰብል 67 በመቶ የሚሆነውም መሰብሰቡንም ገልጿል፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ልማት አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ ድረስ ሳሕሉ(ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በዘንድሮው ዓመት 333 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ ለማልማት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 250 ሺህ ሄክታሩ በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ሥራው በእቅዱ መሠረት በአግባቡ እየተከናወነ የታረሱ መሬቶችን በዘር መሸፈንም ተጀምሯል ያሉት ድረስ ሣሕሉ (ዶ/ር)፤ ክልሉ ላይ ያጋጠመው የፀጥታ ችግር ሥራዎች በሚፈለገው መጠን እንዳይሄዱ እንቅፋት ቢፈጥርም ሰላም ለማስከበር ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በክልሉ የመስኖ አውታር ባልተዘረጋባቸው አካባቢዎች ከ3 ሺህ 100 በላይ ሞተር ፓምፖች ተገዝተው

በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ8 ዞሯል



ድረስ ሣሕሉ (ዶ/ር)



አቶ ልጅዓለም ካሕሣይ

# በትግራይ ክልል 32 ወረዳዎች ድርቅና የምግብ እጥረት አጋጥሟል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል 32 ወረዳዎች ላይ የከፋ ድርቅና የምግብ እጥረት ማጋጠሙን የትግራይ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የትግራይ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ግብረ መልስ አስተባባሪ አቶ ልጅዓለም ካሕሣይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ 32 ወረዳዎች የከፋ ድርቅ እና የምግብ እጥረት አጋጥሟል፡፡

በትግራይ ክልል ደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ መካከለኛውና ሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች የከፋ የድርቅ አደጋ ያጋጠማቸው መሆኑን አቶ ልጅዓለም ተናግረዋል፡፡

አጠቃላይ ክልሉ በጦርነቱ ምክንያት፤ በዝናብ እጥረት በግብርናውም ቢሆን ወቅቱን

በትግራይ ክልል ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል







# ‹‹ተወዳዳሪ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመፍጠር በዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ ሲያመጣ የሚችል የሪፎርም ንቅናቄ ማድረግ ያስፈልጋል››

**- ወይዘሮ ሎሚ በዶ**
**የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ**

**ሞገስ ተስፋ**

አዳማ፡- ተወዳዳሪ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለመፍጠር በዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የሪፎርም ንቅናቄ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ሎሚ በዶ ገለጹ።

በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሪፎርም ንቅናቄ አስፈላጊነትና አተገባበር ላይ ያተኮረ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ሰሞኑን በአዳማ ተካሂዷል።

በመድረኩ መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት ወይዘሮ ሎሚ፣ መንግሥት ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ነድፎ እየሠራ ነው። በተለይም ደግሞ የሀገራችን ዋነኛ የእድገት ምንጭ በሆነው የግብርና ዘርፍ ላይ ትላልቅ ግቦችን በማስቀመጥ ከሁሉ በላይ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ ከውጭ ገቢ ምርቶችን ለመተካትና የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ ሰፋፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

እንደ አፈጉባኤዋ ንግግር፣ የኅብረት ሥራ ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ገጽታን የተላበሰና በመርሕ የሚመራ እራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡ ማኅበራቱ



ለተቋማዊ፣ መዋቅራዊ፣ የሕግ፣ የክትትል፣ ቁጥጥር ክፍተት እንዲሁም በአባላት በማኅበረሰብና በባለድርሻ አካላት ዘንድ የግንዛቤና አመለካከት ውስንነት ከመኖሩ ሌላ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሕጋዊ ማዕቀፍ፣ አደረጃጀት፣ አመራርና አሠራር ክፍተቶች በመኖሩ እድገት እንዳይኖር አድርጓል።

በዚህም ሳቢያ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች መሠል ሀገራት አንጻር የገበያ ድርሻቸውና ተፅዕኖ ደረጃቸው ዝቅተኛ ነው ያሉት ም/አፈጉባኤዋ፤ በተጨማሪም በግብርና ኢንዱስትሪ አገልግሎት ዘርፎች የሚያደርጉት ተሳትፎ የአባሎቻቸውን ፍላጎት ማርካትና ተጠቃሚነታቸውን በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ በሚችሉበት ቁመና ላይ መገኘት አልቻሉም ብለዋል።

እንደ አፈጉባኤ ሎሚ ማብራሪያ፤ በተቋማቱ የአደረጃጀት፣ የአሠራር፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያዎች ለማምጣት በሚያደርገው የሪፎርም ንቅናቄ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡፡ ዓለማ አቀፍ ዓውዱ ካለበት አሁናዊ ሁኔታ እና ከሀገራዊ የፖሊሲ ለውጥ አንጻር ተወዳዳሪ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመፍጠር በዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የሪፎርም ንቅናቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ንቅናቄው የኅብረት የሪፎርም ሥራ የካፒታል አቅማቸውን ለማጠናከር፣ የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ተሳትፏቸውን ለማሳደግ፣ የሀገር ውስጥና የውጪ ገበያ ድርሻቸውን ለማሻሻልና እሴት በሚጨምሩ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ኅብረተሰብ ማዕከል ሆነው እንዲያገለግሉ ለማስቻል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ(ዶ/ር) እንደገለጹት፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የገበያ ትስስር፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ በተለያዩ ጊዜያት ለሕዝብ ችግር መፍቻ ሆነው አገልግለዋል። ይሁን እንጂ አሁንም የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ክፍተት፣ ጠንካራ ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ጋር ተዳምሮ ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓል።

የሪፎርም ሥራው ማኅበራቱ ሊግ እንዲመሠርቱ፣ የቁጠባና የብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲኖሩ፣ ጠንካራ አደረጃጀት እንዲኖር ለማስቻል መሆኑን የገለጹት ም/አፈጉባኤዋ፤ ሪፎርሙ በክልሎች ከስያሜና አደረጃጀት ጀምሮ የሚስተዋለውን የአደረጃጀት ችግር ይመልሳል ብለዋል። በቀጣይ የተጀመረውን የሪፎርም ሥራ ከግብ በማድረስ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱን የሚመጥን ሥራ ይሠራል ብለዋል።

ከ110 ሺ በላይ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ ከ28 ሚሊዮን በላይ አባላት፣ አምስት ፌዴሬሽኖችና 403 ዩኒኖችን አቅፎ ይዟል። ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታልም አስመዝግበዋል፡፡



# የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባላት ደም ለገሱ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አባላት "ደም በመለገስ ሕይወት እንታደግ" በሚል መሪ ሃሳብ የደም ልገሳ መርሐ ግብር በትናትናው ዕለት አካሄዱ፡፡ ወጣቶች በበጋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተግባር በመሳተፍ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባም ተጠቁሟል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብልጽግና ፓርቲ የዲሞክራሲ ባሕል ግንባታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ የኋላእሸት በቀለ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ወጣቶች በበጋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተግባር በመሳተፍ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል፡፡

የተደረገው ደም ልገሳ የበጋ በጎ ፍቃድ አገልግሎት አካል መሆኑን ገልጸው ይህም በደም እጥረት ምክንያት የሚሞቱ ዜጎችን ለመታደግ ትልቅ ሚናው ይኖረዋል።

የመዲናዋ ወጣቶች በክረምት ወራት የተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሲያከናውኑ መቆየታቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፤ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ በበጋ ወቅትም ለመድገም በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የመዲናዋ ወጣቶች የበጎ ፍቃድ ሥራዎች በመሳተፍ ከተማ አስተዳደሩ በሚያከናውናቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ወጣቶች ወደ ጥፋት ከሚወስዱ መንገዶች ነፃ በመሆን የመዲናዋን ዘላቂ ሰላም ብሎም ሀገራዊ አንድነትን በሚያጠናክሩ አስተሳሰቦች ላይ የራሳቸውን ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

የደም ልገሳው የሕዝቦችን አንድነት ለማጠናከር እንደሚረዳ ጠቁመው መርሐ ግብሩ በቀጣይ በሁሉም ክፍለ ከተሞች እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ አባተ በበኩሉ፤ በደም ልገሳ መርሐ ግብሩ ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ዩኒት ደም ይሰበሰባል ብሏል፡፡

ሊጉ የወጣቱን በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑንም አቶ መለስ ጠቁሟል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዋንኛ ዓላማው የአብሮነትና የመረዳዳት ባሕልን ማጠናከር መሆኑን ገልጾ፤ የደም ልገሳው በደም እጥረት ምክንያት የሚፈጠረውን ሞት ለመቀነስ ያግዛል ብሏል፡፡

በደም ልገሳ መርሐ ግብሩ ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ የአዲስ አበባ ወጣቶች እየተሳተፉ እንደሚገኙ ገልጸው፤ መላው የመዲናዋ ወጣቶች በበጋ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሳተፉ አቶ መለስ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊን ጨምሮ የሊጉ አመራሮችና አባላት ተገኝተዋል፡፡

# በመዲናዋ ከ35 ሺህ በላይ ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ሊያደርጉ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት 35 ሺህ 341 ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ እንደሚያደርጉ የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሰብሃዲን ሡልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ በሀገር ደረጃ 70 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ የሥራ ላይ ልምምድ የሚያደርጉት 49 ሺህ ያህሉ የአዲስ አበባ ሲሆኑ 21 ሺህ ደግሞ በክልሎች የሚገኙ ወጣቶች ናቸው፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም 35 ሺህ 341 ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ያደርጋሉ ብለዋል፡፡

ወጣቶቹ በሁለት ሺህ 176 ተቋማት ገብተው ለስድስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድ ያደርጋሉ ያሉት አቶ ሰብሃዲን፤ ለዚህም ለትራንስፖርት አገልግሎት ሁለት ሺህ 420 ብር ይሰጣቸዋል ብለዋል።

እንደየተቋማቱ ሁኔታና የወጣቶቹ ብቃት ከስድስት ወር በኋላም ሊቀጠሩ የሚችሉበት ዕድል አለ ያሉት አቶ ሰብሃዲን፤ መርሐ ግብሩ የአምስት ዓመት የጊዜ ቆይታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሰብሃዲን ገለፃ፤ በሀገሪቱ በየዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት ወደ ሥራ ገበያው ይገባል። ይህንን መመለስ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ወጣቶችን መደገፍና ሥራ የሚፈጥሩ የግል ባለሃብቶችን ማበረታታት ያስፈልጋል።

በተለይም በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ትምህርታቸውን በዩኒቨርሲቲ፣ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብተው መማር ያልቻሉ ወጣቶችን የሚያግዝ ፕሮጀክት ተቀርፆ ወደ ሥራ መገባቱ ለተያዘው ለዜጎች ሥራ ዕድል የማመቻቸት ትግበራ አጋዥ መሆኑን አቶ ሰብሃዲን ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ለሚኖሩ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለማመቻቸትና ከግሉ ዘርፍ ጋር ለማስተሳሰር እየተሠራ ያለው ሥራ ውጤታማ እንደሆነም ተናግረዋል።

እስከ አሁን የተሠሩ ሥራዎችን መገምገምና ለቀጣይ ትግበራ ውጤታማነት ማነቆዎች የመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሆነም ገልጸዋል።

# ኮሚሽኑ የኢትዮ-ራሺያን ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር ትልቅ ፋይዳ አለው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ-ራሺያ የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትርና የኢትዮ-ራሽያ የጋራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ዶክተር በለጠ ሞላ ገለጹ፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ያዘጋጀው የኢትዮ-ራሽያ የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ውይይት በትላንትናው እለት በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

በዚሁ ወቅት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትርና የኢትዮ-ራሺያ የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ሰብሳቢ በለጠ ሞላ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያና ራሽያ በንግድ፣ በቴክኖሎጂ፣ በባሕልና በሌሎች ዘርፎች ስላላቸው ግንኙነት የጣምራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ውይይት በየዓመቱ መከናወኑ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ሚኒስትሩ አክለውም፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ከዚህ ቀደም የአፍሪካ-ራሽያ የመሪዎች ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የተፈረሙ ስምምነቶችና አዲስ ለስምምነት የሚያበቁ ጉዳዮች የደረሱበትን ደረጃ ለመገምገም ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መርሐግብር መሆኑን አንስተዋል፡፡

ሀገራቱ እምቅ ሃብት ቢኖራቸውም በተለይም በንግድና ኢንቨስትመንት ዙሪያ ባላቸው አቅም ልክ እየሠሩ ባለመሆኑ ትብብሩን ለማሳደግ ከዚህ የበለጠ መሥራት እንዳለባቸው ያነሱት ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ በግብርና፣ በአምራችና በማዕድን ዘርፎች ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ መኖሩን ጠቁመው የሩስያ ባለሃብቶች እነዚህን እድሎች ተጠቅመው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ሁለቱ ሀገራት በተያዘው ዓመት አምስት ስምምነቶችን መፈራረማቸውን ለአብነት ጠቁመው፤ ስምምነቶቹ ሀገራቱ በጋራ ለመበልጸግ የያዙትን ውጥን ከግብ ለማድረስ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑንም ነው ሚኒስትሩ የጠቀሱት፡፡

ኢትዮጵያ ለሩሲያ ኩባንያዎች በአግሮ ፓወር፣ በንፋስ ኃይል ማመንጫ፣ በጂኦተርማል ኢነርጂ፣ በተፈጥሮ ጋዝ እና በፀሐይ ኃይል በመንግሥትና በግሉ አጋርነት አዲስ የኃይል ማመንጫ ግንባታ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

እንደ ኑክሌር ሕክምና፣ ቴሌ፣ ጤና፣ ስፔሻሊቲ እና ልዩ የጤና አገልግሎቶችን የመሳሰሉ የላቀ የጤና ቴክኖሎጂዎችን በማዳበር እና ለመጠቀም በጋራ በመሥራት ላይም አጽንዖት እናደርጋለን ብለዋል።



ኢቭጌኒ ፔትሮቭ

ከሩሲያ ጋር በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት፣ በቴክኖሎጂ፣ በሳይበር ወንጀል ምርመራ፣ በኤሮስፔስ ቴክኖሎጂዎች፣ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ በአይሲቲ መሠረተ ልማት ማስፋፊያና አስተዳደር ዘርፎች ኢትዮጵያ በጋራ ለመሥራት ዝግጁ እንደሆነች ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሟን እውን ለማድረግ በትክክለኛው የኢኮኖሚ ጎዳና ላይ እንደምትገኝም ሚኒስቴሩ አብራርተዋል።

የሩሲያ የማዕድን ሀብት ኤጀንሲ ኃላፊ ኢቭጌኒ ፔትሮቭ በበኩላቸው ሩስያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ፍላጎት እንዳላት ተናግረዋል፡፡

በሀገራቱ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ ባለፉት ዘጠኝ ወራት መሻሻል ማሳየቱን ጠቁመው፤ በሌሎች መስኮችም ግንኙነቱ የበለጠ እየዳበረ እንደሚሄድ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

የሩስያ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ያለውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ኢንቨስት ማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እንደሚሠሩም አስታውቀዋል፡፡

ውይይቱም በሁለትዮሽ የንግድ እንቅስቃሴ ተለዋዋጭነት፣ የሩሲያ እና የኢትዮጵያ ትብብር የሕግ ማዕቀፍ መሻሻል፣ ለሠላማዊ ዓላማ አቶሚክ ኢነርጂ መጠቀም ላይ፤ ኢንዲሁም በሳይንስ፣ በትምህርት መስክ እና በሌሎች ዘርፎች ላይም በጋራ ለመሥራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው።

በትናንትናው እለት በሁለቱ ሀገራት መካከል የቢዝነስ ፎረም የሚካሄድ ሲሆን፤ በዚህም የኢትዮጵያና የራሽያ በርካታ ኩባንያዎች ተገናኝተው ቀጣይ አብሮ መሥራት በሚችሉባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች ዙሪያ የሚመካከሩበት እንደሚሆን ተገልጿል፡፡



በለጠ ሞላ(ዶ/ር)

በውይይቱ በኢትዮጵያ የሩሲያ አምባሳደር ኢቭጌኒ ተርኪሂን፣ ከሩሲያ የመጡ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ባለሀብቶች ተሳትፈዋል፡፡

# በከተማዋ ከ65 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፤- በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት አምስት ወራት ለ 65 ሺ 255 ዜጎች በቋሚነት የሥራ እድል መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ ።

በቢሮው የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ሰብሃዲን ሡልጣን በተለይ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በዓመት ሁለት ጊዜ የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ይከናወናል።

ዘንድሮ በመጀመሪያው ዙር 128 ሺ 680 ሥራ ፈላጊዎችን ከሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች በአንድ ማዕከል እንዲመዘገቡ ተደርጓል ያሉት አቶ ሰብሃዲን፣ ለዚህም 138ሺ ሥራ ሊፈጠርባቸው የሚችሉ መደቦችን የመለየት ሥራም ተከናውኗል ብለዋል። በዚህም ለ 65 ሺ 255 ዜጎች ቋሚ ሥራ መፍጠር የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ ሴቶች ናቸው።

በአጠቃላይም ከ75 በመቶ በላይ ወጣቶች ሲሆኑ ሦስት ነጥብ ሁለት በመቶ የሚሆኑት ከዩኒቨርሲቲና ከሌሎች የትምህርት ተቋማት የተመረቁ መሆናቸውን አቶ ሰብሃዲን ጠቁመው፤ የተሰማሩባቸው የሥራ መስኮችም በዋናነት በአገልግሎት፤ በኮንስትራክሽን፤ በማኑፋክቸሪንግ፤ በከተማ ግብርና መሆኑንና በቀዳሚነት ትልቁን ድርሻ የሚይዙት የአገልግሎትና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም ከተማ አስተዳደሩ ወጣቶች ዝቅተኛ ክፍያ እንዳይከፈላቸው ብቁ ሆነው ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማስቻል ከዓለም ባንክ ጋር በመሆን «ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ» የተሰኘ ፕሮጀክት እየተገበረ ይገኛል ብለዋል።

ለዚህም 30 ሺ የሚደርሱ ሥራ አጦች የተመዘገቡ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 15 ሺ 341 ለቀጣይ ስድስት ወራት በየወሩ 2 ሺ 420 ብር የትራንስፖርት ክፍያ እየተሰጣቸው ወደ ልምምዱ እንደሚገቡ ጠቁመዋል፡፡

ልምምዱ የሚደረግባቸው 2 ሺ 176 ተቋማትም መለየታቸውንና በፕሮጀክቱ የሚካተቱት እድሜያቸው ከ18 እስከ 25 ዓመት ብቻ የሆኑ የትምህርት ደረጃቸውም ከ12ኛ ክፍል በታች የሆኑ ገበያው ላይፈልጋቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ እንደሆኑና ከእነዚህም ውስጥ 60 በመቶ ሴቶች እንደሚሆኑ ተናግረዋል ።

ይህም ሆኖ ሁሉም ሥራ አጥ ሥራ ይፈልጋል ማለት አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ደመወዙ ዝቅተኛ ነው በማለት፤ ሥራ በማማረጥ፤ በአጭር መንገድ ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት በማሳየት በርካቶች ለሥራ ዝግጁ እንዳልሆኑም ገልጸዋል።

በመሆኑም ቢሮው ይህንን ችግር ለመቀነስ የሚያስችል የአመለካከት ለውጥ ለመፍጠር ከሴቶችና ሕጻናት፤ ከማኅበራዊ ጉዳዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# ኤጀንሲው በአምስት ወራት ከ175 ሺህ በላይ ልደትና ሞት መዘገበ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ ፡- የአዲስ አበባ የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ በአምስት ወራት ውስጥ በመዲናዋ 175 ሺህ 557 ልደትና ሞት መመዝገብ መቻሉን አስታውቋል።

ኤጀንሲው በ73 የመንግሥትና የግል የጤና ተቋማት ሲካሄድ የነበረውን የልደትና የሞት ወቅታዊ ምዝገባ ያለበትን ደረጃ በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትላንትናው እለት ተወያይቷል ።

የአዲስ አበባ የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ዓለማየሁ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በከተማዋ ያለው የወቅታዊ ምዝገባ ሽፋን ቅድሚያ የሚሰጠው በጤና ተቋማት ለሚከሰቱ ሁነቶች ሲሆን እነዚህም ልደትና ሞት ናቸው፡፡

ኤጀንሲው ላለፉት ዓመታት የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎችን ሲመራ ቆይቷል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ ሆኖም ከተቋማዊ ሪፎርሙ በኋላ ቢሮ ውስጥ ሲሰጥ



አቶ ዮናስ ዓለማየሁ

የነበረውን የምዝገባ አገልግሎት በጤና ተቋማት ላይ እንዲሰጥ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በጤና ተቋማት ቢሮ ከፍቶ የመመዝገቡ ሥራ በሀገሪቱ የመጀመሪያው ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ምዝገባ የሚካሄድባቸው የጤና ተቋማትን 73 ደርሰዋል፡፡ በዚህም በከተማዋ ከፍተኛ ልደትና ሞት የሚከሰትባቸው የጤና ተቋማት ላይ የምዝገባ ሽፋኑን በማስፋት ከተማዋን




ወይዘሮ ቤተልሔም ታደሰ

ዘመናዊ የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት እንዲኖራት ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

በ2017 ዓ.ም የከተማዋን የምዝገባ ሽፋን መቶ በመቶ ለማድረስ ታቅዷል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ ይህ ማለት ከተማዋ ላይ የሚወለድ ማንኛውም ሕጻን እንዲሁም የሚሞት ሰው የሚመዘገብ ይሆናል ብለዋል፡፡ ማኅበረሰቡ ሞት ሲከሰት መጥቶ የማስመዝገብ ባሕሉ ዝቅተኛ በመሆኑ የሞት ምዝገባ ላይ የሚታይ ክፍተት አለ ሲሉም አክለዋል።

በኤጀንሲው የመረጃ ማስረጃ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ ቤተልሔም ታደሰ በበኩላቸው፤ ኤጀንሲው በ2017 ዓ.ም የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎትን በማዘመን ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ለመሆን አልሞ እየሠራ ነው። በዚህም በጤና ተቋማት የሚደረገውን የምዝገባ ሽፋን ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቷል ብለዋል።

ኤጀንሲው 2015 ዓ.ም ከ76 ሺህ 500 በላይ ልደትና ሞት መመዝገብ ችሏል ያሉት ወይዘሮ ቤተልሔም በዚህ ዓመት በተሠራ ጠንካራ ሥራም በአምስት ወራት ውስጥ 169 ሺህ 77 ልደት እንዲሁም ስድስት ሺህ 481 ሞት መመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

በቀጣይም ሁሉም የጤና ተቋማት ላይ ምዝገባ እንዲጀምሩ የማድረግ፣ ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት ፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በተለያዩ ተቋማት ላይ አሠራር ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ እንዲሁም ለጤና መዋቅር ሰፊ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአዲስ አበባ ሕገ ወጥ ተግባራትን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥል!

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብሎም አፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ የሆኑ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑባት ነው፡፡ ከተማዋ በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት የሚያበቋት የተለያዩ መሠረተ ልማቶችና የመዝናኛ ሥፍራዎች በስፋት እየተከናወኑባት ይገኛሉ፡፡

የአዲስ አበባን ገጽታ የሚቀይሩና እና የቱሪስት ፍሰት የሚያሳድጉ ሥራዎችንም በመሥራት ከኢትዮጵያ አልፋ የአፍሪካ መዲና የሆነችው ከተማ በጎብኚዎች ተመራጭ ሀገር እንድትሆን የተሠራውም ሥራ የብዙዎችንም ቀልብ የገዛ ነው፡፡ በገበታ ለሸገር ፕሮጀክት የአንድነት፣ የወንድማማችነትና የእንጦጦ ፓርኮች ከአዲስ አበባ አልፈው የሀገር ኩራት ለመሆን በቅተዋል፡፡ በአዲስ አበባ የተሰሩት አመርቂ ሥራዎችም ኮይሻን፣ ጎርጎራንና ወንጪን ለመሳሰሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች መነሻ ሆነዋል፡፡

ሆኖም እንደስሟ አዲስ እየሆነች የመጣችው አዲስ አበባ ከእድገቷ ጎን ለጎን በጸጥታ ችግርና በሕገ ወጥ ተግባራት መበራከት በመፈተን ላይ ትገኛለች፡፡ ሰዎችን አግቶ ገንዘብ መጠየቅ፣ የቡድን ዝርፊያ፣ በሞተር ሳይክል ንጥቂያ፣ ባጃጅና የራይድ ታክሲዎችን ተጠቅሞ ሰው መግደል፣ ሞባይል መንጠቅ፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያና የተደራጀ ከባድ የዝርፊያ ወንጀል እና የመሳሰሉት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡

የሺሻ ማስጨሻ፣ የጭፈራና የቁማር ቤቶች እንዲሁም ሕገ-ወጥ የንግድ ሱቆችም ለሕገ ወጥ ተግባራትና ወንጀል መስፋፋት የበኩላቸውን አሉታዊ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ከወረዳ ጀምሮ በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችም ሌላ የአዲስ አበባ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ከመታወቂያ አሰጣጥ ጀምሮ በደንብ ማስከበር፣ በቤቶች አሰጣጥ፣ በግንባታ ፍቃድ፣ በመሬት አቅርቦትና በመሳሰሉት ዘርፎች የሚስተዋሉ ችግሮች በግስጋሴ ላይ የምትገኘውን ከተማ ወደ ኋላ ሰቅዘው የሚይዟት ናቸው፡፡

በየስርቻው እንደ አሸን የፈሉትም ቁማር ቤቶች የወጣቱን የወደፊት ተስፋ እያጨለሙትና የነገ ሀገር ተረካቢ በሆነው ትውልድ ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደረ ነው፡፡ በስፖርት ውርርድ ስም ወጣቱ ጊዜውን በቁማር እንዲያሳልፍና የወደፊት ሕይወቱን በአግባቡ እንዳይመራ የሚያደርጉ ሕገ ወጥ ተግባራት በአዲስ አበባ በሁሉም አካባቢ ተንሰራፍቶ መመልከቱ ልብን የሚሰብር ነው፡፡

ከእነዚህ ችግሮች ባሻገር በተለይ በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነቱን ከተገቢው በላይ የሚያጦዙና ከኅብረተሰቡ ችግር ማትረፍ የሚፈልጉ ስግብግብ ነጋዴዎችም የአዲስ አበባ ሕዝብ ሸክሞች ናቸው። በኅብረተሰቡ ላይ የኑሮ ጫና እየፈጠሩ የሚገኙ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች በሰዓታት ልዩነት የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር በማድረግ ኅብረተሰቡን ለምሬት ከመዳረጋቸውም በላይ በሕዝብና በመንግሥት መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡

ሕገ ወጥነት እና የጸጥታ ችግር በተስፋፋበት ሁሉ ሰላም ይደፈርሳል፣ ሕግ ይዛባል፣ የዜጎች በሰላም ወጥቶ መግባት ይስተጓጎላል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ሕገ ወጦችና ሙሰኞች ምቹ መደላደል ይፈጠርላቸዋል። እንደልባቸው ሕዝብን እያማረሩ ሀብት ያጋብሳሉ፣ መደላድላቸውን ያጠናክራሉ፣ የሴራ ገመዳቸውን ያጠብቃሉ፡፡ ስለዚህም እነዚህን ሕገ ወጦችንና ሕገ ወጥ ተግባራትን ሳይዘናጉ ማስተዋልና ችግሮች ተፈጥረው ሲገኙም ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማሳወቅና አጥፊዎችም የእጃቸውን እንዲያገኙ ማድረግ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ ግን መንግሥት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገትን የማፋጠን ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ ሕገ ወጥ ተግባራትን እየተከታተሉ ማረምና የጸጥታ ችግሮችን ማስወገድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ሀገር የተረጋጋ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲኖር፣ ዜጎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮቻቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማከናወን ሲችሉ በመሆኑ የኅብረተሰቡን በሰላም ወጥቶ የመግባት ሂደት የሚያውኩትን እየተከታተሉ ርምጃ መውሰድ የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ አንጻር ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ የሚታየውን የጸጥታ ችግርና ሕገ ወጥ ተግባራትን ፈር ለማስያዝ የጸጥታ አካላት በቅንጅት የወሰዱት ርምጃ የሚበረታታና ተጠናክሮም ሊቀጥል የሚገባው ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሀገራዊ ስጋት እየሆነ የመጣው የኮንትሮባንድ ንግድ

ፍሬሕይወት አወቀ

በአንድ ሀገር ውስጥ ጤናማ የሆነ የንግድ ሥርዓት መፍጠር ከተቻለ የዜጎችን የመልማት ጥያቄ በተገቢው መመለስ ይቻላል፡፡ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ማሻሻልና ማሳደግም ከባድ አይሆንም፡፡ በተመሳሳይ በአንድ ሀገር ጤናማ የንግድ ሥርዓት ባልሰፈነ ጊዜ እንዲሁ ሕገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ፣ የንግድ ሥርዓትን በማዛባት የሀገር ኢኮኖሚን በእጅጉ ይጎዳል፡፡

ይህም በዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር እና የሀገር ደኅንነት አደጋ በመሆን ጭምር የነገ ተስፋን ያጨልማል፡፡ በሀገሪቱ ያለው ዕውነታም ይህው ነው።

ምክንያቱም በኢትዮጵያ ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል፡፡ ይሄንን የሚከውኑ ሕገ ወጥ አካላትም እንዲበራከቱ፣ የኮንትሮባንድ ዓይነቱም ፈርጀ ብዙ እየሆነ መጥቷል። እነዚህ አካላትም ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ያለአግባብ ሀብት ማፍራት ሲችሉ መመልከት ተለምዷዊ ተግባር ሆኗል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ አደጋ የደቀነ ስለመሆኑ በስፋት ይነሳል፡፡ ለዚህም በየጊዜው ከጉምሩክ ኮሚሽን የሚወጣው መረጃ ዕውነታውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ሕገ ወጥና የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል ከሚያደርገው ጥረት ባለፈ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ እያደረሰ ያለው ኪሳራ እንዲሁም የደቀነው አደጋ እጅግ አደገኛና ፈታኝ መሆኑን በየጊዜው ይገልጻል፡፡ ለምሳሌ፣ ኮሚሽኑ በ2015 በጀት ዓመት ብቻ 80 ቢሊዮን ብር የተገመቱ የተለያዩ የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶችን በቁጥጥር ስር እንደዋለ መግለጹ ይታወሳል፡፡

በቅርቡ ባወጣው መረጃ ኮሚሽኑ ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል እያደረገ ባለው ጥረት የመንግሥት ሹማምንት እንቅፋት እንደሆኑበት አቤቱታውን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቧል። ይሄንንም፣ «የማዕድናት እና የሌሎች ሸቀጦች ሕገ ወጥ ንግድ ከመንግሥትም ከፌዴራል ፖሊስም አቅም በላይ ሆኗል» ሲሉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቤቱታቸውን ያቀረቡት የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ ናቸው።

የኮንትሮባንድ ንግድ በላዕላይ የመንግሥት ክፍል መፍትሔ የሚያሻ ጉዳይ እንደሆነም ኮሚሽነሩ መናገራቸውን ነው የመገናኛ ብዙኃን የዘገቡት። በተለይ በማዕድን ዘርፍ ያለውን ሕገ ወጥ ንግድ የሚከላከል ራሱን የቻለ የፀጥታ ኃይል እንደሚያስፈልግም ኮሚሽነሩ ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ወርቅ እና ሌሎችም ውድ ማዕድናት "ጥቁር መንገድ" ተብለው በሚጠሩ ጎዳናዎች ከሀገር እንደሚወጡ ነው የተገለጸው፡፡ እነዚህ ጎዳናዎች በፀጥታ ኃይሎች ከለላ የሚደረግላቸው እንደሆነና ከበርካታ የመንግሥት ተቋማትም ድጋፍ የሚያገኙ እንደሆነ በመጥቀስ፣ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ሲያዙ የመንግሥት ሹማምንት ሰዎቹንም አብሯቸው የተያዘውንም ሸቀጥ ልቀቁ በማለት ጫና የሚያሳድሩም ስለመኖራቸው ነው የተገለጸው፡፡ ሕገ ወጥ ነጋዴዎችን በመያዛቸው ለእስር የተዳረጉ የጉምሩክ ሠራተኞች ስለመኖራቸውም ኮሚሽኑ ለፓርላማው ባቀረበው አቤቱታ ተጠቅሷል፡፡

ታዲያ ኮሚሽኑ እንደገለጸው፣ በተለያዩ ዘርፎች እንደ አሸን ፈልቶ የምናስተውለው ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ፣ ለሆዳቸው ባደሩ የመንግሥት ሹማምንቶች ድጋፍ ያለው ነው፡፡ ለዚህም ማሳያዎቹን አንድ ሁለት ብሎ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለአብነትም ህልቆ መሳፍርት የሌለው አልባሳትና ሸቀጣሸቀጥ ህጋዊ የመግቢያና የመውጫ ሰነድ ሳይኖረው፣ ታክስ ሳይከፈልባቸው፣ ድንበር ጥሶ፣ ኬላ በጣጥሶ ከሀገር ሀገር ይዘዋወራል፡፡

ማንም ጠያቂ የሌለው በመሆኑም እንደልቡ ይገባል ይወጣል፡፡ ለዚህም በመቶ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኙት የንግድ ሱቆች አፍ አውጥተው ይናገራሉ። በተለይም ሕጋዊ ከሆኑ የንግድ ሱቆች በላይ በየጥጋጥጉ ልባሽ ጨርቆችን፣ መጫሚያዎችንና ሌሎች ቁሳቁሶችንም አሰማምረውና አበጃጅተው የያዙ ቦንዳ ቤቶችን ላስተዋለ የነጻነታቸውን ጥግ መረዳት አያዳግትም፡፡

እነዚህ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ታዲያ ሕጋዊና ግብር ከፋይ የሆነውን ነጋዴ በኪሳራ ከገበያ እንዲወጣ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሲፈጥሩ እየተስተዋለ ነው፡፡ የሥራ አጥ ቁጥር በየጊዜው እንዲጨምር በማድረግ ባለሀብቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል በሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ምክንያት ድርጅቶች ይዘጋሉ፣ ሠራተኛ የነበሩ ዜጎችም ሥራ አጥ ለመሆን ይገደዳሉ፡፡ ይህም በመንግሥት ላይ ጫና የሚፈጥርና ኢኮኖሚውን የማዳከም አቅሙ የላቀ ነው፡፡

ታዲያ ችግሩ በዚህ መልኩ የሚገለጸው ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ፣ በጊዜው መልክ ካልያዘና ካልተገታ መዘዙ ከዚህም በላይ የሀገር ስጋትነቱም ማደጉ አይቀሬ እንደመሆኑ ለችግሩ መቃለል መሥራት ለነገ የማይባል ተግባር ነው። ይሄን ማድረግ ግን የአንድና የሁለት ነጋዴዎችና የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጉዳይ ሳይሆን የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ሊሰመርበትና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑ የግድ ነው፡፡

ለዚህም መንግሥት ትልቁን ድርሻ በመውሰድ እንደ ሀገር የተጋረጠበትን አደጋ በጥሞና ሊከታተለውና ዛሬ እልባት ሊያበጅለት ካልቻለ ነገ እንደ ሀገር ሊያጠፋን የተዘጋጀ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ለዕድገትና ለልማት ጸር የሆነው ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሚያሳድረው ተጽዕኖ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡

ለአብነትም፣ የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ በማድረግ ሕዝቡን ያማርራል፡፡ የበዛ ምሬት ደግሞ አደጋው የከፋ ይሆናልና እንደ ሀገር ሊያጠፋን እየተንደረደረ ያለውን ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ መከላከል የግድ ይላል፡፡ ኮንትሮባንድ የማይገባበት ቦታና የማያጠቃልለው የሸቀጥ ዓይነት ባለመኖሩ በተለይም በሰዎች ጤና ላይ ለሚያስከትለው አደጋ ትልቅ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የኮንትሮባንድ ነጋዴ ዋነኛ ግቡ ለመንግሥት መክፈል ያለበትን ታክስ ሳይከፍል በነፃ ለማሳለፍ፣ የገበያ ተወዳዳሪነት መርህና የሀገሪቱን ሕግ በመጣስ ትርፍ ማጋበስ ነው፡፡ የፍተሻ ኬላዎችን ጥሶ በማለፍ ዕቃውና ሰነዱ እንዳይመሳከር በማድረግ ከተጠያቂነት ማምለጥ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ኮንትሮባንድ ንግድ የደራበት ዋናው ምክንያት ምንድነው ብሎ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

«ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ» እንዲሉ አበው፣ የሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ መነሻና መዳረሻውን በውስጡ የሚያልፉ አካላትን ጭምር በፍጹም በቁርጠኝነት፣ በብርቱ ጥረትና ርብርብ ለይቶ መድፈቅ የግድ ይላል፡፡

ባለፉት አራት ወራት ብቻ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ከሀገር ሊወጡ የነበሩ፣ እንዲሁም ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ገደማ ግምት ያላቸው ወደ ሀገር ሊገቡ የነበሩ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን የጉምሩክ ኮሚሽን መያዝ ችሏል፡፡ ይህ ቁጥር ታዲያ ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንጻር ሲታይ ገና ብዙ መሥራትን የሚጠይቅ ነው፡፡ እናም እያንዳንዳችን የልማት፣ የብልጽግናና የሰላም ፀር የሆነውን ሕገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ልንዋጋውና ልንጸየፈው ይገባል፡፡

# ያለ ካርታ 52 ዓመታትን የዘለቀው ገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

### መነሻ ሃሳብ

ገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ይባላል፤ ስድስት ኪሎ አንበሳ ጊቢ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፤ ዛሬ ላይ 500 የሚጠጉ ሕጻናትና ታዳጊዎችን እውቀት እየመገበ ያለ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እና ሞዴል የሚባል ስለመሆኑ የሚያውቁት ይመሰክሩለታል፤ ይሄንኑ የሚያረጋግጡ ሰነዶችንም ያቀርባሉ፡፡

ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቱ በዘመናት ጉዞው ውስጥ የእኔ የሚለው ካርታና ፕላን የለውም፤ ካርታና ፕላን በስሙ እንዲዘጋጅ ተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም መልስ ግን ማግኘት አልተቻለም፤ ይሄም ለትምህርት ቤቱ ሕልውና ስጋት ፈጥሯል፤ በመማር ማስተማር ሂደቱም ላይ ጫና አሳድሯል፤ በመሆኑም የሚመለከተው አካል ችግሩን ተገንዝቦ የዘመናት ጥያቄው ምላሽ ያገኝ ዘንድ ለሕዝብ ጆሮ፤ ለመንግሥትም ዐይን አድርሱልን የሚል ጥያቄ ወደ ዝግጅት ክፍላችን ደረሰ፡፡

እኛም ይሄንኑ ጥያቄ መነሻ በማድረግ በቦታው በመድረስ እና የሚመለከታቸውን በማነጋገር፣ ሰነዶችን በመፈተሽም የጥያቄውን ተገቢነት በመገንዘብ ለዛሬው የፍረዱኝ ዐምድ ጥንቅራችን መርጠነዋል። እናም በዚሁ ጉዳይ ላይ በማተኮር፤ ትምህርት ቤቱ ለምን ካርታና ፕላን አልተሰራለትም፤ ይሄ አለመሆኑስ ምን ጫና ፈጠረበት፤ በቀጣይስ ችግሩን ለመፍታት ምን ታስቧል፤ የሚሉና መሰል ጉዳዮችን በማንሳት ስለ ጉዳዩ የሚያስረዱ በሰነድና በሰው ማስረጃነት ያገኘናቸውን መረጃዎች በማጠናቀር አቅርበናል፡፡

### ገነት አጸደ ሕፃናት ት/ቤት ማነው?


ትምህርት ቤቱ በ1964 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ተቋቁሞ እየሰራ የቆየ ሲሆን፤ የደርግ መንግሥት መምጣቱን ተከትሎ በአዋጅ መሰረት ከ1967 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም የህዝብ ተቋም ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ ይሁንና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን በ3ኛው መደበኛ ስብስባ በሰጠው ውሳኔ መሰረት፤ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከህዝብ ወደ መንግሥት ይዞታነት እንዲዛወሩ ህዝቡ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ተደረገ፡፡

ከዚህ በኋላም በ2004 ዓ.ም መጨረሻ በአዋጅ የህዝብ ተቋማት ወደ መንግሥት እንዲዛወሩ በተወሰነው መሰረት፤ የገነት አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት ወደ መንግሥት ተቋም ተዛውሮ እንደማንኛውም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እንደሚደረገው አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅትም 500 የሚጠጉ ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ቤት እየተማሩ ይገኛሉ፡፡

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያሳዩትም፤ ይህ ትምህርት ቤት ከኤምባሲዎች፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ተቋማት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት የፈጠረ ሲሆን፤ ሞዴል የሚያሰኙት አሰራርና ግብዓቶችን ያካተተ ነው፡፡ 1ሺ800 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው ትምህርት ቤቱ ምንም እንኳን በዚህ ደረጃ ሞዴል ቢሆንም፤ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የለውም፤ ማስተር ፕላንም አልወጣለትም። ይሄም በመማር ማስተማር ሂደቱ፤ እንዲሁም በትምህርት ቤቱ የነገ እድገትና ተስፋ ላይ ትልቅ ፈተና ስለመሆኑም ነው የሚመለከታቸው አካላት ያስረዱት፡፡

### የትምህር ቤቱ ውሎች?

**የትምህርት ቤቱ አመሰራረትና አስተዳደርም ምንም ዓይነት ውል ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር አለመፈራሙን ያብራራል፡፡ ቀደም ሲልም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ሲጠየቁ እንደነበርም ከፅሁፉ መረጃዎች መረዳት ተችሏል**


በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
የሰው ኃይል አስተዳደር
ክትትል ድጋፍና መረጃ
ዋና የሥራ ሂደት
✉ 25227

Arada Sub-city Administration
Human Resource Administration
Monitoring, Evaluation an Inforemat
Core Pross
☎ 0118 96 35 33

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለ ገነት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት
አዲስ አበባ

ቁጥር [illegible]
ቀን 11/12/04

ጉዳዩ፣ ከህዝብ ወደ መንግስት ለተዛወሩ ት/ቤቶች የመደብ መታወቂያ ቁጥርና ደረጃ ሰጥቶ መላክን ይመለከታል፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢፌዲሪ ሚኒስትሮች ም/ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን በ3ኛው መደበኛ ስብሰባ በሰጠው ውሳኔ መሰረት የህዝብ ት/ቤቶች ከህዝብ ወደ መንግስት ይዞታነት እንዲዛወሩ ህዝቡ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ገልፆ ውሳኔ ከተሰጠባቸው 102 ት/ቤቶች ውስጥ ለ53ቱ የአፀደ ህጻናት ት/ቤቶች ደረጃና የመደብ መታወቂያ ቁጥር እንዲሰጥለት በቀን 21/11/04 በቁጥር አ9/253/አ28-40/35 በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቁን ገልጾ ለስራ መደቡ በተጠየቀው መሰረት ደረጃና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ሰጥተው መላካቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቁጥር 11m11-05/10/101 በቀን 02/12/04 ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ የጸደቀውን ደረጃና የመደብ መታወቂያ ቁጥር 1 ገጽ እያይዘን እየላክን ተገቢው እንዲፈጸም እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
ለአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ
በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለአቅም ግንባታ ጽ/ቤት
አዲስአበባ

የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት በርካታ ውሎችን ሲዋዋል ራሱን የቻለ ህጋዊ ተቋም ሆኖ ነው። ለአብነትም፣ ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በተለያዩ ወቅቶች ውል አስሯል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት እንደ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም የሚጠበቅበትን ማህበራዊ ኃላፊነት ሲወጣ የቆየ ሲሆን፤ ለአብነትም የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ቦንድ መግዛትና የመሳሰሉትንም ሲወጣ ስለመቆየቱ ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በተረፈ ይህ ትምህርት ቤት ከማንኛውም ሦስተኛ ወገን ወይንም ትምህርት ቤቱን አሊያም አጸደ ግቢውን አስተዳድራለሁ ከሚል አካል ጋር የተፈራረመው ህጋዊ ፊርማ አለመኖሩን ማወቅ ተችሏል፡፡ ወይንም ትምህርት ቤቱ ውል ሲዋዋል የነበረው በራሱ ሥም ነው፡፡

### የአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽ/ቤት

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽህፈት ቤት በቀን 22/08/2011 ዓ.ም በቁጥር አ/ክ/ከ/ወ/6/ትም/ስል/ቤት/134/2011 ዓ.ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጉዳዩ፤ የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት የካርታ ጥያቄን የሚመለከት ደብዳቤ ፅፏል፡፡

የደብዳቤው ፍሬ ሃሳብም፣ በቀድሞው ወረዳ 13 በንዑስ ቀበሌ 03 በአዲሱ የወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር የሚገኘው የቤ.ቁ 1371 የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ለአራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ማናጅመንትና ይዞታ ማረጋገጫ ጽህፈት ቤት ማመልከቱን ያብራራል፡፡

ነገር ግን የይዞታ ማረጋገጫ ጽህፈት ቤቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ይዞታውን እንደሚያስተዳድረው ስለገለፀ ካርታ መስጠት አንችልም የሚል መልስ እንደተሰጠው በመጠቆም፤ ካርታ ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነም ይጠቁማል፡፡ ይሁንና «በጽህፈት ቤቱ የተሰጠው መልስ ትክክለኛ ነው ብለን አናምንም» በማለት ያብራራል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽህፈት ቤት እንደሚለው ከሆነ፤ ትምህርት ቤቱ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ ከተመሰረተ ጀምሮ ምንም ዓይነት ክፍያ ከፍሎም አያውቅም። የትምህርት ቤቱ አስተዳደሮችም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ወይንም በተለምዶ አጠራር (ኪ.ቤ.አ.ድ) ጋር ምንም እውቅና እንደሌለው ያስረዳል፡፡

እንደ ማብራሪያው፣ ትምህርት ቤቱ በ1964 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ተቋቁሞ እየሰራ የቆየ ሲሆን፤ የደርግ መንግሥት በመምጣቱ ተከትሎ በአዋጅ መሰረት ከ1967 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም የህዝብ ተቋም ሆኖ እየሰራ ቆይቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ግን በ2004 ዓ.ም መጨረሻ በአዋጅ የህዝብ ተቋማት ወደ መንግሥት እንዲዛወሩ በተወሰነው መሰረት፤ የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ወደ መንግሥት ተቋም ተዛውሮ እንደማንኛውም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እንደሚደረገው አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡


በመሆኑም ይህ ነባር ትምህርት ቤት ካርታ ሊያስከለክለው የሚችል አንዳችም ምክንያት አለመኖሩን፤ የትምህርት ቤቱ አመሰራረትና አስተዳደርም ምን ዓይነት ውል ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር አለመፈራሙን ያብራራል፡፡ ቀደም ሲልም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ሲጠየቁ እንደነበርም ከፅሁፉ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽህፈት ቤት በ02/01/2011 ዓ.ም በቁጥር አ/ክ/ከወ/6/ትም/ስል/ ጽ/ቤት/1161/2011 ዓ.ም የገነት አፀደ ሕፃናትን ትምህርት ቤት ካርታ ይመለከታል በሚለው ደብዳቤው፤ ትምህርት ቤቱ በመንግሥት ሥር እየተዳደረ የሚገኝ ተቋም ሆኖ እያለ ህጋዊ ካርታ አለማግኘቱን ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ቢሮው በዚህ ጉዳይ ላይ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

## ያለ ካርታ 52 ዓመታትን...



አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጽ/ቤት

Arada Sub-City Wereda 6 Administration Education and Training office

Tel- 011-1-26-29-16

Addis Ababa

ቁጥር፡- አ/ክ/ከ/ወ/6/ትም/ስል/ጽ/ቤት/134/2011ዓ.ም

ቀን-22/08/2011 ዓ.ም

ለአራዳ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡የገነት አጸደ ህጻናት ት/ቤት ያካርታ ጥያቄ ይመለከታል

ከላይ በርእሱ ለመግጽ እንደተሞከረዉ በቀድሞዉ ወረዳ 13 በንኡስ ቀበሌ 03 በአዲሱ የወረዳ 06 አስተዳደር ትም/ት ጽ/ቤት ስር የሚገኘዉ የቤ.ቁ 1371 የገነት አጸደ ህጻናት ት/ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ለአራዳ ክ/ከተማ መሬት ማናጅመንት ይዞታ ማረጋገጫ ጽ/ቤት ማመልከታችን ይታወቃል፡፡ነገር ግን የይዞታ ማረጋገጫ ጽ/ቤቱ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የፌድራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ይዞታዉን እንደሚያስተዳደረዉ ስለገለጸልን ካርታ መስጠት አንችልም የሚል መልስ ሰጥቶናል፡፡ነገር ግን ጽ/ቤቱ የሰጠዉ መልስ ትክክለኛ ነዉ ብለን አናምንም፡፡ምክንያቱም ት/ቤቱ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ ከተመሰረተ ጀምሮ ምንም ዓይነት ክፍያ ከፍሎም አያዉቅም፤የት/ቤቱ አስተዳደሮችም ከኪ.ቤ.ድ ጋር ምንም እዉቅና እንደሌለዉ ያስረዳሉ፡፡ማለትም በ1964 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ተቋቁሞ እየሰራ የደርግ መንግስት በመምጣቱ በአዋጅ መሰረት ከ1967 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም የህዝብ ተቋም ሁኖ እየሰራ መሆኑን ቆይቷል፡፡ከዚህ በኋላ በ2004 ዓ.ም መጨረሻ በአዋጅ የህዝብ ተቋማት ወደ መንግስት እንዲዛወሩ በተወሰነዉ መሰረት የገነት አጸደ ህጻናት ት/ቤት ወደ መንግስት ተቋም ተዛዉሮ እንደማንኛዉም የመንግስት ት/ቤቶች እንደሚደረገዉ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ለመረጃ ያክል በወረዳ 06 አስተዳደር ዋና ስራ አስፋጻሚ እና ቤቶች ልማት ተወክሎ የነበረ ሃላፊ የጻፈዉን ደብዳቤ አብረን ያያዝን ሲሆን ጥያቄያችን እንዲመለስልን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ግልባጭ

ለአራዳ ክ/ከ/ትም/ት ጽ/ቤት

ለወረዳ 06 ትም/ት ጽ/ቤት

ለገነት አጸደ ህጻናት

አዲስ አበባ

ከሰላምታ ጋር

ታረቀኝ ደሳለኝ አበበ

TAREKEGN DESALEGN ABEBE

የአ/ክ/ከ/ወ/6 ት/ም/ጽ/ቤት ኃላፊ

**ከገጽ 6 የዞረ**

ትኩረት ሰጥቶና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መፍትሄ እንዲሰጥ ሲል ጠይቋል፡፡

### የወረዳ 06 አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽህፈት ቤት፣ ለአራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ማናጅመንት ጽህፈት ቤት በቀን 30/08/2009 ዓ.ም በቁጥር አ/ክ/ከ/ወ6/ዋ/ስ/አ/640/09 መረጃ መስጠትን ይመለከታል በሚል በጻፈው ደብዳቤው፤ በክፍለ ከተማው ወረዳ 06 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 1371 (ገነት አጸደ ሕፃናት) ወረዳው የሚያስተዳድረው ስለመሆኑና አለመሆኑ መረጃ መጠየቁን በመጥቀስ ማብራሪያና መረጃ ሰጥቷል፡፡

በዚህም መሠረት፤ በቁጥር አ/ክ/ከ/ወ6/ኮ/ቤ/ል 665/08 በቀን 27/05/08 የተፃፈው ደብዳቤ የተሻረ መሆኑን እየገለጽን የቤት ቁጥር 1371 የገነት አፀደ ሕፃናት ትምህርት ቤት መሆኑንና ወረዳው የማያስተዳድረው መሆኑን ከፋይል በማጣራት ያረጋገጥን በመሆኑ የመንግሥት ይዞታ መሆኑን እንገልፃለን ሲል የመንግሥት ትምህርት ቤት መሆኑን ያስረዳል፡፡

### የወረዳ 06 ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት በአራዳ ክፍለ ከተማ በመሬት እና ማንጅመንት ጽህፈት ቤት ለይዞታ አስተዳደርና የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት በ2009 ዓ.ም በቁጥር አ/ክ/ከ/ወ/6/ቤ/ል/2001/2009 በፃፈው ደብዳቤ በወረዳው የሚገኘውን የቤት ቁጥር 1371 የሚያስተዳድረው ስለመሆኑና አለመሆኑ መረጃ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ደብዳቤ መሰረትም፤ የቤት ቁጥሩ 1371 የገነት አፀደ ሕፃናት ትምህርት ቤት መሆኑን፤ ወረዳው የማያስተዳድረው ከፋይል መጣራቱን ይልቁንም የመንግሥት ይዞታ ስለመሆኑም ያብራራል፡፡

### አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት እና ማናጅመንት ጽህፈት ቤት

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፅህፈት ቤትም በዚህ ትምህርት ቤት ጉዳይ በርካታ ደብዳቤዎችን ሲፃፃፍ የቆየ ቢሆንም፣ እልባት አልተገኘም፡፡ ለአብነትም በ2/09/2009 ዓ.ም በቁጥር አ/ክ/ከ/ወ6/ዋ/ስ/ጽ/ቤት/643/2009 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ስለመጠየቅ በሚል ደብዳቤ ፅፏል። ፍሬ ሃሳቡም፣ የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት በመንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር ስለመሆኑ የሚጠቅስ ሲሆን፤ የይዞታ ማረጋገጫ አስፈላጊነትና ይህም ለትምህርት ቤቱ እንዲሰጥ የሚል ነው። ይህ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው አካላት ግልባጭ ቢደረግም ምላሽ እስካሁን መፍትሄ አልተሰጠውም፡፡

### የአራዳ ክፍለ ከተማ የሰው ኃይል አስተዳደር

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የሰው ኃይል አስተዳደር ክትትልና ድጋፍ መረጃ ዋና የሥራ ሂደት በቁጥር አ/ክ/ከ/ሰ/ኃ/አ/ክ/ድ/00/05 በቀን 11/12/04 ዓ.ም ከህዝብ ወደ መንግሥት ለተዛወሩ ትምህርት ቤቶች የመደብ መታወቂያ ቁጥር እና ደረጃ ሰጥቶ መላኩን በማስመልከት፤ ለገነት ትምህርት ቤት የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል፡፡

‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢፌዴሪ ሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን በ3ኛው መደበኛ ስብስባ በሰጠው ውሳኔ መሰረት የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከህዝብ ወደ መንግሥት ይዞታነት እንዲዛወሩ ህዝቡ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ገልፆ፤ ውሳኔ ከተሰጠባቸው 102 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለ53ቱ የአጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች ደረጃና የመደብ መታወቂያ እንዲሰጥለት በቀን 21/11/04 በቁጥር አ9/253/አ28-40/35 በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቁን ገልፆ ለሥራ መደቡ በተጠየቀው መሰረት ደረጃና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ሰጥተው መላካቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቁጥር 11ጠ11-05/10/101 በቀን 02/12/04 ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ የጸደቀውን አያይዘን እየላክን ተገቢው እንዲፈጸም እናሳስባለን›› ሲል፤ በግልባጭ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እና ለአቅም ግንባታ ጽህፈት ቤት አሳውቋል፡፡

### ወላጆች እና የት/ቤቱ ማህበረሰብ

የወረዳ 06 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አበራ አጌና እንደሚሉት፤ የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ለበርካታ ዓመታት በመማር ማስተማር ውስጥ ያለፈ እና ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ያስቆጠረ ታሪካዊ ተቋምና አንጋፋ ባለሙያዎችን ያፈራ ነው፡፡

በተለይም ደግሞ ይህ ትምህርት ቤት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጭምር በትምህርት ጥራት፣ በግቢ ፅዳት፣ በተቋም አደረጃጀትና እንደ ትምህርት ቤት ሁሉን አቀፍ የሆነ ብቃት በከፍተኛ ደረጃ የያዘ ስለመሆኑ የተመሰከረለት ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በርካታ ትምህርት ቤቶች ምርጥ ተሞክሮ ለመቅሰም ሲሉ ወደዚህ ትምህርት ቤት በየጊዜው ጎራ እንደሚሉ ይናገራሉ፡፡

በተጨማሪም ትምህርት ቤቱ በከተማ አቀፍ በርካታ ሽልማቶች ጭምር የተሰጡትና ሞዴል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ምንም እንኳን ትምህርት ቤቱ በዚህ ደረጃ የገዘፈ ሥም ቢኖረውም የይዞታ ካርታ አለማግኘቱ ሚስጥር እንዳልገባቸው ይናገራሉ። እርሳቸውም ሆኑ ከእርሳቸው ቀደም ብለው በወረዳው የነበሩ አመራሮች በተደጋጋሚ በዚህ ጉዳይ ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ያሳወቁና የጉዳዩን አንገብጋቢነት ያሳሰቡ ቢሆንም፤ ምላሽ እንዳላገኙና ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ መሆኑንና በተለይም መሰል ጉዳዮች ከወረዳው አቅም በላይ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት በዚህ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሲያገለግሉ የቆዩ መሆናቸውን የሚናገሩት አንዲት መምህርት፤ ትምህርት ቤቱ በየጊዜው የተለያዩ ፈናዎችን በማለፍ ዛሬ ላይ መድረሱን ይናገራሉ፡፡ በተለይም ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ቁልፍ የሚባሉ ፈተናዎች በማለፍ በአሁኑ ወቅት ተመራጭ ትምህርት ቤት መሆኑን ያወሳሉ፡፡

እርሳቸው በዚህ ትምህርት ቤት የመንግሥት ተቀጣሪ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቱም የመንግሥት ስለመሆኑ በተለያዩ ወቅቶች ከተሰነዱ ሰነዶች መረዳታቸውን፤ በመንግሥታዊ ስብሰባም ትምህርት ቤቱን ወክለው የሚሳተፉ አመራሮች መኖራቸውንና አሁንም ድረስ በዚሁ የቀጠለ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሆኖም የገነት አፀደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ለምን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደማያገኝ እንቆቅልሽ ነው ይላሉ፡፡

ሥማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ሌሎች የትምህርት ቤቱ መምህራን በበኩላቸው፣ ትምህርት ቤቱ ግማሽ ክፍለ ዘመን ያስቆጠረ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ የተመሰረቱት በርካታ ትምህርት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ። ይሁንና አያሌ ምሁራን ያፈራው የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ካርታ የለውም ወይንም አልተዘጋጀለትም ማለት ምን ማለት ነው? ሲሉም ይጠይቃሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚሰሙ ጭምጭምታዎች በትምህርት ቤቱ ላይ ሌላ አካል የእኔ ነው በሚል በይገባኛል ጥያቄ ካርታ ማውጣቱንና ይህም ለትምህርት ቤቱ አደጋ መደቀኑ አይቀሬ እንደሆነ ስጋታቸውን ይናገራሉ። በተለይም ቦታው ስድስት ኪሎ እምብርት ላይ በመሆኑ የበርካቶች ዓይን ማረፊያ ነው፡፡ በመሆኑም ህልውናውን ሊያጣ የሚችልበት ዕድል ሊኖር ስለሚችል መንግሥት አፋጣኝ መፍትሄ ሊሰጠውና ትምህርት ቤቱ ወደተሻለ ምዕራፍ እንዲሸጋገር ይገባል ሲሉም ይማፀናሉ፡፡

### ሌሎች ቆየት ያሉ ሰነዶች፡-

**ሰነድ አንድ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ የዞን 4 ትምህርት መምሪያ በ1994 ዓ.ም በቁጥር ዞ4/4/226/76/48 ለአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ‹‹ጉዳዩ የዕድሳት ፈቃድ ይመለከታል›› የሚል ደብዳቤ ጽፏል። በዚህ ደብዳቤም በዞን 4 መምሪያ ሥር በወረዳ 13ቀበሌ 03 በቤት ቁጥር 1371 የሚገኘው ወ13 ቀ03 አጸደ ሕፃናት የፈቃድ ዕድሳት በጠየቁን መሰረት የትምህርት መምሪያችን ከስታንዳርድ ገምጋሚ ኮሚቴ በ09/05/94 ቦታው ድረስ በአካል በመገኘት ከገመገመ በኋላ አመልካች አብዛኛውን አፀደ ሕፃናት መስፈርቶችን ያሟላ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ፈቃዳቸውን ቢያድስላቸው የማንቃወም መሆኑን እንገልፃለን ሲል የጻፈ ሲሆን፤ በግልባጩም ለዞን 4 ትምህርት መምሪያ ክፍል ለወረዳ 13 ቀበሌ 3 አጸደ ሕፃናት ወይንም በአሁኑ አጠራር ለገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት አሳውቋል፡፡

ሰነድ ሁለት፡- በቀድሞ አጠራሩ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ሙአለ ሕፃናት ትምህርት ቤት በአሁኑ አጠራር ደግሞ የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት በተመለከተ በ1973 ዓ.ም በከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የከፍተኛ 13 ቀበሌ፤ 03 ጽህፈት ቤት በቁጥር 03/522/73 ለከፍተኛ 13 ቀበሌ፤ 03 ሂሳብ ክፍል የፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል፡፡

‹‹ቀበሌያችን ተረክቦ እንዲያስተዳድር የተደረገው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ሙአለ ሕፃናት ትምህርት ቤት እየተባለ ለሚጠራው ሥራ ሁኔታ የቀበሌው ሥራ አመራር ኮሚቴ በ12/5/73 ዓ.ም ጠቅላላ ስብሰባ አድርጎ ትምህርት ቤቱን ለሙአለ ሕፃናት አገልግሎት የተሟላና ስራውን ማንቀሳቀስ እንዲችል ለሥራ ማስኬጃ ብር 500 ወጪ ሆኖ እንዲከፈል መፍቀዱ›› ይታወሳል፡፡ በመሆኑም ለሥራ ማስኬጃ ገንዘቡ ወጪ እንዲደረግና ሥራው እንዲፋጠን የሚያሳስብም ጭምር ነው፡፡

### የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት

አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ወንድወሰን ባንጃው በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ የጠየቅናቸው ሲሆን፤ ጉዳዩ የተለያዩ አካላት ፍላጎትና ጥያቄ ያለበት በመሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን ለመስጠት ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ገልጸውልናል፡፡ ዝግጅት ክፍሉም የእርሳቸውን እና ሌሎች ጥያቄ ያላቸውን አካላት ምላሽና ማብራሪያ በቀጣይ ይዞ የሚቀርብ መሆኑን ከወዲሁ ለመግለጽ ይወዳል፡፡

# በትግራይ ክልል 32 ወረዳዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያልጠበቀ ዝናብና የድርቅ አደጋ በማጋጠሙ አብዛኛው የክልሉ ነዋሪ እርዳታ ፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

አስተባባሪው እንዳሉት፤ በክልሉ የተከሰተው የድርቅ አደጋ በዋነኝነት በጦርነቱ እና ከተፈጥሮ ጋር ተያይዞ የድርቅ አደጋ በመከሰቱ ያጋጠመ ነው፡፡

ያጋጠመው የምግብ እጥረት አደጋ ለአንድ ዓመት ያህል በትኩረት ርዳታ እንደሚያስፈልግ በመግለፅ፤ መንግሥት በቅርቡ ርዳታ እንደሚልክ ቃል በገባው መሠረት በፍጥነት ወደ ተረጂው እንዲዳረስ ይደረጋል ብለዋል፡፡

ክልሉ ላይ ያለውን ሀብት በማጥናት ቀጣይነት ያለው የልማት ሥራዎችና የመልሶ ግንባታ ሥራዎች በማጠናከር ውጤታማ ወደ ሆነ ሥራ መግባት የግድ ነው ሲሉም ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት አቶ አታለለ አቡሐይ እንዳሉት፤ በመጪዎቹ ሦስት ቀናት ለሦስተኛ ዙር የሚሰራጭ ርዳታ እንዳለ አመላክተዋል፡፡

ርዳታው በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በድርቅና በግጭት ችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች ይከፋፈላል ብለዋል፡፡

በትግራይ ክልል ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በድርቅና በግጭት ምክንያት ለምግብ እጥረት መጋለጣቸውን ያነሱት አቶ አታለለ፤ ክልሉ ያጋጠመው አደጋ ከአቅሙ በላይ እንደሆነ ባሳወቀው መሠረት ርዳታው ለሚያስፈልጋቸው የክልሉ ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር፣ ዋግኽምራ፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ሰሜን ሸዋ አካባቢ፣ በምሥራቅ ጎጃም እንዲሁም በአፋር ክልል ወደ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዜጎች በድርቅ እና በሰው ሠራሽ ችግሮች የምግብ እጥረት ማጋጠሙን አንስተው፤ አስፈላጊው ርዳታ ለነዚህ አካባቢዎችም እንደሚሰራጭ ጠቅሰዋል፡፡

# በሶማሌ ክልል ለሽብር ጥቃት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጅግጅጋ፣ ፊቅ፣ ዋርዴር እና ቢኬ አካባቢዎች እንደነበርም ነው የተገለጸው፡፡

የጋራ ግብረኃይሉ ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የሽብር ጥቃት ለመፈጸም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 14 የአልሸባብ የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን አስታውቋል፡፡

በሶማሊያ የሰላም ማስከበር ተልዕኮውን በብቃት በመወጣት ላይ በሚገኘው ጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊት ተደጋጋሚ ሽንፈትና ኪሳራ የደረሰበት የአልሸባብ የሽብር ቡድን አባላትን በህቡዕ በመመልመልና በማደራጀት በሶማሌ ክልል በጅግጅጋ ከተማ እና በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የሽብር ጥቃት በመፈፀም ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳቶችን ለማድረስ ዕቅድ አውጥቶ ለመንቀሳቀስ ቢሞክርም ሴራው ሙሉ በሙሉ መክሸፉን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ አስታውቋል።

አልሸባብ በህቡዕ አደራጅቶና ተልዕኮ ሰጥቶ የላካቸው 14 የቡድኑ አባላት ሊጠቀሙባቸው ካዘጋጇቸው ተቀጣጣይ ቁሶችና የተለያዩ ሰነዶች ጋር በቁጥጥር ስር የዋሉት በኢትዮጵያና በሶማሊያ ድንበር ሾልከው ወደ ሶማሌ ክልል ዘልቀው በመግባት በጅግጅጋና በሌሎችም የክልሉ ከተሞችና አካባቢዎች ዒላማዎችን በመለየት የሽብር ጥቃት ለመፈፀም ዕቅድ አውጥተው ሲንቀሳቀሱ መሆኑን መግለጫው ጠቁሟል።

በሕግ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ከተደረጉት ከእነዚህ ተጠርጣሪዎች መካከል አሊ አብዲ በቅፅል ስሙ መዓሊን አሊ በመባል የሚታወቀው የሽብር ቡድኑ መሪና አስተባባሪ መቀመጫውን ሶማሊያ ካደረገው የአልሸባብ ክንፍ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በሶማሌ ክልል ውስጥ ሆኖ የሽብር ቡድን አባላትን በማደራጀት፣ በመገናኘት፣ በመመልመል፣ የሽብር እቅድ በማውጣትና ዒላማዎችን በመለየት ጥቃቶች እንዲፈፅሙ የሥልጠናና የሎጀስቲክስ ድጋፎችን ሲያደርግ ከሌሎች 13 ግብረ አበሮቹ ጋር በተካሄደው የተቀናጀ ክትትል በሞያሌ ከተማ የመግቢያ ኬላ በኩል ሾልኮ ለመውጣት ሲሞክር በቁጥጥር ሥር መዋሉን የጋራ ግብረ- ኃይሉ መግለጫ አመልክቷል፡፡

አልሸባብ የሽብር ጥቃቶችን እንዲፈጽሙ ስምሪት የሰጠው በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ፊቅ፣ ዋርዴር እና ቢኬ አካባቢዎች እንደነበር ያመለከተው መግለጫው÷ የህቡዕ አደረጃጀት በመፍጠር የሽብር ተልዕኮ ለመፈጸም የተንቀሳቀሱት ተጠርጣሪዎች ለሽብር ጥቃቶች ሊጠቀሙባቸው ካዘጋጇቸው በርካታ ክላሽንኮቭ መሣሪያዎች፣ ጥይቶች፣ ሽጉጦች፣ ቦንቦች፣ ተቀጣጣይ ቁሶችና የተለያዩ ሰነዶች ጋር መያዛቸውን አስታውቋል፡፡

በተጨማሪም የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይሉ በሶማሌ ክልል በሲቲ ዞን ምኤሶ ወረዳ፣ ፋፋን ዞን ጅግጅጋ ከተማና ዙሪያው፣ ዶሎ ዞን ዋርደር ከተማና ዙሪያው፣ ቆራሄ ዞን ህግሎሌ ወረዳ እና ኤረር ዞን ፊቅ ከተማ ባካሄደው ተከታታይ ኦፕሬሽኖችና የአሰሳ ሥራዎች የሽብር ቡድኑ ለጥቃት ሊያውሏቸው የነበሩ 84 ክላሽንኮቭ መሣሪያዎች፣ 10 የቡድን መሣሪያዎችና 12 ሽጉጦች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ መደረጉን መግለጫው አክሎ ገልጿል።

በተለይም አልሸባብ በኢትዮጵያ ላይ ዒላማ ያደረገውን የሽብር እኩይ ሴራና ጥቃት ለማሳካት የፈንጅ መቀመሚያ ንጥረ ነገሮች በህቡዕ ባደራጃቸው ህዋሶች አማካኝነት በሕገ ወጥ መንገድ በኢትዮጵያ ድንበር ወደ ደቡብ ሶማሊያ በማጓጓዝ ላይ እያለ በኤረር ዞን ጋሻሞ ወረዳ በቁጥጥር ሥር እንዲውል መደረጉን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ባወጣው መግለጫ አያይዞ ጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ከሶማሊያና ሌሎች አጎራባች ክልሎች ጋር ሰፊ ድንበር የሚጋራ በመሆኑ የአልሻባብ የሽብር ቡድን ሐሰተኛ መታወቂያዎችና ፓስፖርቶችን እንዲሁም ሌሎች ሰነዶችን በመጠቀም አባላቶቹን ወደ ኢትዮጵያ አስርጎ በማስገባት በመሠረተ ልማቶችና የነዳጅ ማጠራቀሚያዎች ላይ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈጸም ተደጋጋሚ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል ያለው መግለጫው፤ ከውጭ አቻ የመረጃ ተቋማት ጋር በሚደረግ የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም እየተካሄዱ ባሉ ጥብቅ ክትትሎችና ኦፕሬሽኖች አማካኝነት የሽብር ሴራዎችንና ተልዕኮዎችን ማክሸፍ መቻሉን የጋራ ግብረ-ኃይሉ ጠቁሟል።

በዚህ አጋጣሚ የሽብር ቡድኑ ሴራዎች እንዲከሽፉ፤ የሶማሌ ክልል መንግሥት የፀጥታ መዋቅር እና የክልሉ ሕዝብ ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅዖ የጋራ ግብረ-ኃይሉ ምስጋናውን አቅርቧል፡፡

በመጨረሻም በመላ ሀገሪቱ የፀጥታና ደኅንነት ስጋቶችን በማስወገድና በሽብር ቡድኖች እንዲሁም በፀረ-ሰላም ኃይሎች የሚታቀዱ የጥፋት ሴራዎችን በማክሸፍ እና በቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማድረግ በኩል የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመቀናጀት እየወሰዱት ያለው እርምጃ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አስታውቋል፡፡

# በአማራ ክልል ከ300 ሺህ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለዞኖች እየተሰራጩ መሆኑን ያመለከቱት ድረስ ሣሕሉ (ዶ/ር)፤ ግብርና ሚኒስቴር ከ12 ሺህ በላይ የውሃ ፓምፕ ገዝቶ ለክልሎች እያከፋፈለ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህም የተጀመረውን ሥራ በማገዝ በኩል ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች በዝናብ መዘግየት ምክንያት ድርቅ ማጋጠሙን አስታውሰው፤ በድርቁ ምክንያት ያልተመረተውን ምርት በመስኖ ልማት ለማካካስ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ክልሉ ላይ በተደጋጋሚ የአፈር ማዳበሪያ እጥረት በችግርነት ሲነሳ እንደነበር ጠቅሰው፤ ፌዴራል መንግሥቱ በዚህ ዓመት ቀደም ብሎ ግዢ ፈጽሟል፡፡ ክልሉም የተመደበለት ማዳበሪያ እየገባ ስለሆነ በኮማንድ ፖስቱ እገዛ በወቅቱ ለአርሶ አደሩ ለማድረስ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እስካሁን ድረስ ለበጋ መስኖ ልማት የሚውል ከ60 ሺህ ኩንታል በላይ ማዳበሪያ መሰራጨቱንም ገልጸው፤ በበጋ መስኖ ልማት ልማት ከ5 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል፡፡

በ2015/16 የመኸር እርሻ ከ5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ሰብል መመረቱን አስታውሰው፤ ከዚህም ከ160 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል፡፡ እስካሁን ድረስም ከ67 በመቶ በላይ የሚሆነው ሰብል ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

የክልሉን ግብርና እንቅስቃሴ የፀጥታ ችግር፣ የማዳበሪያ እጥረትና ድርቅ ፈትነውት እንደነበር ገልጸው፤ ችግሮችን ለመቅረፍ ከተሠራው ሥራ ጎን ለጎን ምርትና ምርማነትን ለመጨመር በተደረገው ርብርብ ጥሩ ውጤት መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡

# ምክር ቤቱ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢነት ሹመታቸው በአንድ ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምፅ ፀድቆ፣ ተሿሚዋ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ-መሐላ ፈጽመዋል።

ትናንት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው የተሾሙት ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ ውልደታቸው በጎንደር ከተማ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ በትምህርት ዝግጅታቸው የመጀመሪያ ዲግሪ በሕግ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪ በሰላም እና ደኅንነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ተጨማሪ ሁለተኛ ዲግሪ በሕዝብ አስተዳደር ከሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ማግኘታቸው ተጠቁሟል፡፡

በሥራ ልምዳቸው በኢትዮጵያ የጉምሩክ ባለሥልጣን ከጀማሪ የሕግ ባለሙያነት አንስቶ የኦፕሬሽን መምሪያ ኃላፊ እና የሕግ አፈጻጸም መምሪያ ኃላፊ በመሆን የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለ10 ዓመታት በትጋትና በታማኝነት መወጣታቸውንም የሕይወት ታሪካቸው ያስረዳል፡፡

ኒውጄነሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅን በማቋቋም የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻውን በመምራት ውጤታማ ያደረጉ ሲሆን ፤ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሴኔት አባል በመሆንም አገልግለዋል፡፡

የግል የሕግ አማካሪ ተቋም በማቋቋም የሥልጠናና የማማከር አገልግሎት፣ የሕግ ሰነዶች ዝግጅት፣ ግልግልና የግልግል አገልግሎት እንዲሁም ለሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስትራቴጂና የፖሊሲ ሰነዶችን በመቅረጽ ሰፊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

ከየካቲት 2012 ዓ.ም እስከ የካቲት 2015 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ከቦርድ አመራሮችና ከመላው ሠራተኛ ጋር በመሆን ምርጫ 2013 እንዲሁም በክልሎች የተካሄዱ ሕዝበ ውሳኔዎችን በብቃት የመሩና በምርጫ ቦርድ የሪፎርም ሥራዎች በብቃት በመሳተፍ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በትናንቱ ውሎው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሹመትን ካፀደቀ በኋላም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ሹመቶችንም መርምሮ አጽድቋል፡፡ በዚህም መሠረት አቶ መሳፍንት ተፈራን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አድርጎ ሾሟል፡፡

ሹመቱን ያቀረቡት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ ቤልጂጌ እንደገለጹት፤ አቶ መሳፍንት ተፈራ በትምህርት ዝግጅታቸው በብሮድካስት ጋዜጠኝነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመርቀዋል፡፡ በሥራ ልምዳቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በዘጋቢነት፤ በሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ማዕከል በእውቀት አስተዳደር ሥርጭት ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ እና ዳይሬክተርነት፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙዩኒኬሽን ኤክስፐርት እንዲሁም ትናንት እስከተሰጣቸው ሹመት ድረስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ምክትል ሥራ አስፈጻሚ በመሆን አገልግለዋል።

ምክር ቤቱ በእለቱ አቶ ጌትነት ታደሰን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ በማድረግም ሾሟል፡፡

አቶ ጌትነት ታደሰ በትምህርት ዝግጅታቸው በታሪክ ትምህርት ዲፕሎማ እንዲሁም በጋዜጠኝነት እና በተግባቦት ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀዋል። ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በጋዜጠኝነት እና ተግባቦት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል።

በሥራ ልምዳቸው በአማራ ማስ ሚዲያ በጋዜጠኝነት ያገለገሉ ሲሆን፣ በዋልታ ሚዲያ እና ኮሚዩኒኬሽን በዶክመንተሪ አዘጋጅነትና በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሠርተዋል። ከ2010 ጀምሮም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን እስከ ትናንትናው እለት ሲያገለግሉ መቆየታቸው ተገልጿል፡፡

# በጥናት ላይ ስተመሠረተ ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዋናነት ከተሰጡት ተልዕኮዎች መካከል የንግድ አሠራርን ማዘመን፣ ግልጽ፣ ተደራሽና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ቀጠናዊ ትስስርን ማጠናከር፣ የውጭ ንግድን ማስፋትና ማሳደግ፣ የዕቃዎችንና አገልግሎት የጥራት ደረጃ ማዘጋጀትና መቆጣጠር፣ የሸማቹንና የንግዱን ማህበረሰብ እንዲሁም የሀገርን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥና የንግድ ሥርዓት መገንባት የሚሉትም ተልዕኮዎቹ ናቸው፡፡

ሚኒስቴሩ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ ቢሆንም፣ አሁንም ድረስ በንግዱ ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ስለመኖራቸው ይገለጻል፡፡ በዘርፉ የሚስተዋሉትን እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት በሚኒስቴሩ በኩል በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፡፡ ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር ለመሥራት የሚያስችለውን ስምምነት በቅርቡ ፈጽሟል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር በጥናትና ምርምር የተደገፈ ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ባደረገበት ወቅት፤ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናትና ምርምር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ደስታው መኳንንት፣ የኢትዮጵያን የንግድ ሥርዓት ተግዳሮቶች በአግባቡ ለመፍታት አስቻይ የሆነው መንገድ ጥናትና ምርምርን መሠረት ያደረገ አሠራር መዘርጋት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የንግድ ጉዳይ በተለያዩ አደረጃጀቶች ሲሰራ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ንግድና ኢንዱስትሪ ይባል ነበር፤ ንግድ ሚኒስቴር ተብሎም የተጠራበት ወቅትም ነበር፤ አሁን ደግሞ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሚል እየተጠራ ይገኛል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ፖሊሲዎች እንዲሁም የንግድና አጠቃላይ ሀገራዊ የጥራት ፖሊሲ አዘጋጅቶ በ2022 የንግድ ዘርፍ በአፍሪካ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት የሚል ራዕይ ሰንቆ እየሠራ ይገኛል፡፡

በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ የአሠራር ለውጦችን ያደረገው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በተጨማሪ 30 የሚደርሱ የተለያዩ መመሪያዎችን በማሻሻል የአሠራር ለውጦችን አድርጓል፡፡ ስታንዳርዶችንም አዘጋጅቷል፡፡ ያም ቢሆን ታዲያ አሁንም ድረስ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓት ለመገንባት ጥናትና ምርምርን የተከተለ ትግበራ ማስፈለጉ እንደታመነበት አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሶስት ትላልቅ ዘርፎች የሚመራ ሲሆን፤ አንደኛው የንግድ ሥርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ የሀገር ውስጥ ንግድና ሸማቾች ጥበቃን ጨምሮ በውስጡ ሁለት ትላልቅ ዘርፎች አሉት፡፡ ሁለተኛው የንግድ ትስስርና ወጪ ንግድ ፕሮሞሽን ዘርፍ ነው፡፡ ይህም ሶስት ትላልቅ ዘርፎችን የያዘ ሲሆን የውጭ ንግድ ግብይት፣ የውጭ ንግድ ፕሮሞሽንና ግብይት ማሳለጥ እንዲሁም የዓለም አቀፍና ቀጣናዊ ትስስር ናቸው፡፡ ሶስተኛው የጥራት መሠረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ ሲሆን፤ በዚህ ውስጥም ሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ይገኛሉ፡፡ እነሱም የሕጋዊ ሥነ ልክና የቴክኒክ ደንብ ማስተባበር፣ የጥራት ማረጋገጫ ሲሆን፣ በገቢና ወጪ ቁጥጥር ላይ ትኩረት አድርገው ይሰራሉ፡፡

ከእነዚህ ሶስት ዋና ዋና ዘርፎች በተጨማሪም የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ከምርምር ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ይሠራል፡፡ ዘርፉ ከፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር በመገናኘት በፖሊሲ መነሻ ሃሳቦች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ይህም በጥናት ላይ የተመሰረቱ የአሰራር ለውጦች እንዲኖሩ ማድረግ ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብርቱ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

በተለይም በግብይት ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን ዛሬም ድረስ መቅረፍ እንዳልተቻለ ጠቅሰው፣ ችግሩ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናትና ምርምርን እንደሚጠይቅ ዶክተር ደስታው አስታውቀዋል፡፡ አሁን ላይ በተለይም በግብይት ሥርዓቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን የመፍታቱ ሥራ ሳይንሳዊ ጥናቶችን የሚጠይቅ፤ የምርምርና የጥናት ተቋማትን እገዛ የሚያፈልግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም የንግድና የጥራት ፖሊሲዎች መዘጋጀታቸውን ጠቁመው፣ በቅርቡ እንደሚጸድቁም ዶክተር ደስታው አስታውቀዋል፡፡ ይህም ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በንግዱ ዘርፍ ትልቅ ችግር ያለባቸውና ጥናትና ምርምር ያስፈልጋቸዋል ብሎ ከለያቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡

ዶክተር ደስታው እንደተናገሩት፤ በንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ በፍትሃዊ የንግድ ውድድር ላይ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ችግሮቹን በጥናትና ምርምር መለየት ያስፈልጋል፡፡ በንግድ ሥርዓቱ ላይ ያሉ ችግሮች፣ የፍትሃዊነት ችግሮችና የሕግ ጥሰቶችን ያጠቃልላሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ ትልቅ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የአሠራር ማሻሻያዎችን የሚጠይቁ ሰፋፊ ሥራዎች ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሀገር ውስጥ ንግድን ማስጀመር ትልቅ አበርክቶ እንዳለው የጠቀሱት ዶክተር ደስታው፤ በዚህ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችንም እንዲሁ በጥናትና ምርምር መለየትና ማጥናት እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በዓለም አቀፍ መለኪያ መሠረት ሚኒስቴሩ የሀገር ውስጥ ንግድ በማስጀመር ሥራ በኩል በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ላይ መሥራት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ትልቅ መሳሪያ መሆን ይችላል፡፡ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አሰጣጥን ለማሳለጥ በርካታ ሥራዎችን የሠራ ቢሆንም፣ በንግድ ማስጀመር ላይ ግን አሁንም በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የብዙ ተቋማትን እገዛና ሚና የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋማትን ለማስተሳሰር በፖሊሲና ጥናት ምርምር ኢንስቲትዩት እገዛ ጥናት ይደረጋል፡፡

በንግድ ውድድርና የሸማቾች መብት ጥበቃ በኩል አሁንም በሸማቾች በኩል ያለው ግንዛቤ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ደስታው፤ ይህም የጥናትና ምርምር ሥራን እንደሚጠይቅ አመልክተዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የመሠረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት ዝንባሌንና ልምዱንም በሚገባ ማጥናት ያስፈልጋል። አሁንም ድረስ መንግሥት በመሠረታዊ ሸቀጥ አቅርቦት ውስጥ ይገባል፡፡ ይህ እስከመቼ ይዘልቃል? ምን ዓይነት የአቅርቦት ሥርዓት ሊኖር ይገባል? የሚል ጥናት ማድረግንም ይጠይቃል፡፡ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የመሠረታዊ ሸቀጥ ፍላጎትንም ከምርቱ ጋር የማስተሳሰር ሥራን መሥራትም ያስፈልጋል፡፡

የአክሲዮን ማህበራት ሕጋዊነት አሠራርን በተመለከተም ጥናት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ የጠቀሱት ዶክተር ደስታው፤ በኤክስፖርት ንግድ ዘርፍ አፈጻጸምም እንዲሁ ሰፊ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ተናግረዋል፡፡ ‹‹በሀገሪቱ በርካታ የኤክስፖርት ምርት ይመረታል፡፡ በሚመረተው ምርት መጠን ልክ ግን የውጭ ምንዛሪ እየተገኘ አይደለም፡፡›› ሲሉ የሚገልጹት ዶክተር ደስታው፣ በዚህ ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በተለይም ከምርት እስከ ውጭ ገበያ ድረስ ያለውን ሂደት በጥናት መለየትና መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

**በሀገሪቱ በርካታ የኤክስፖርት ምርት ይመረታል፡፡ በሚመረተው ምርት መጠን ልክ ግን የውጭ ምንዛሪ እየተገኘ አይደለም። በዚህ ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በተለይም ከምርት እስከ ውጭ ገበያ ድረስ ያለውን ሂደት በጥናት መለየትና መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል**

የግብርና ወጪ ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነት ላይ ክፍተት ስለመኖሩ አንስተው፤ ብዙ ምርቶች በሚጠበቀው የጥራት ደረጃ ላይ አለመሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ይህም ማለት አብዛኞቹ የግብርና ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ አይደሉም ማለት እንዳልሆነም ገልጸው፣ ጉዳዩ በጥናትና ምርምር ከሚፈልጉ ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የገቢና የወጪ ንግድ ምርት ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ችግሮች እንዳሉበትም አመልክተዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅትም በአቅርቦትና ፍላጎት መሀል ያለው ልዩነት ስለሰፋ በአቅርቦት ላይ ትልቅ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ቢሆንም በንግድ ሥርዓቱ ላይ ትልቅ ችግር እየፈጠረ ያለው የምርት ጥራትን የማስጠበቅ ጉዳይ ነው›› ያሉት ዶክተር ደስታው፤ ጥራትን በዘላቂነት ለማስቀጠል የጥናትና ምርምር ሥራ የግድ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ የምርት ጥራትን ለማሳደግ መሠረተ ልማት ከማሟላት በተጨማሪ ተጠቃሚው ለጥራት የሚሰጠው ዋጋ መጨመር እንዳለበት አስታውቀው፣ ማህበረሰቡ ለጥራት ያለው ዕይታ የተስተካከለ እንዲሆን መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ በበኩላቸው እንዳሉት፤ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍና የንግድ ሥርዓቱን በማዘመን በሀገሪቱ ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓት ለመገንባት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ነው፡፡ ጥረቶቹን ውጤታማ ለማድረግም ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ መድረሱ አንድ ርምጃ ሲሆን፣ በዚህም በርካታ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ስለተሳለጠ የንግድ ሥርዓት፣ ስለሸማቾች መብት ጥበቃ፣ ስለወጪ ምርቶች እድገት፣ ስለመዳረሻ ገበያ ውጤት እንዲሁም ከጥራት አንጻር የኢትዮጵያ ምርት በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለሚገኝበት የተወዳዳሪነት ሁኔታ፣ ሰው ባወቀው ልክ ከሚሰጠው ምክረ ሃሳብ ይልቅ ደረጃውን በጠበቀ ጥናትና ምርምር ሊገለጽ ይገባል። በንግድ ሥርዓቱ ዙሪያ በዘፈቀደ የሚሰጡ ሃሳቦችና ችግሮችን የሚገልጹ አስተያየቶች ስለመኖራቸው ሚኒስትሩ ጠቅሰው፤ እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚለየው፣ መፍትሔ የሚሰጠውና የሚያረጋግጠው የጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት እንደሆነ ገልጸዋል።

ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ጥናት ችግሩን መለየትና ተቀባይነት ያለውን መፍትሔ ማቅረብ ይቻላል ያሉት ሚኒስትሩ፤ እንደ ሀገር በንግድ ሥርዓቱ ላይ ሰፋፊ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙ አመልክተዋል። ስምምነቱ እነዚህን ውስብስብ ችግሮች ግልጽ በሆነ የጥናትና ምርምር ምክረ ሃሳብ ለመፍታት ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ የተቋሙን ሥራዎች የበለጠ ተቋማዊ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ሥራ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል።

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በበኩላቸው፤ ኢንስቲትዩቱ የመንግሥትን ሥራ ለሚያከናውኑ ተቋማት በፖሊሲ ጉዳዮች በምርምር የተደገፈ እገዛ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ብዙ ጎልቶ የወጣ እንዳልነበረ ጠቅሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ በርካታ ጥናትና ምርምሮችን እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በንግድ ሥርዓት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከኢንስቲትዩቱ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን በመሥራት ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን ማግኘት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ከኢንስቲትዩቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባላቸው የሥራ መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ፤ ውጤቱንም ለባለድርሻ አካላት በመስጠትና በማስተቸት ምክረ ሃሳብ እንዲቀርብ ይደረጋል። በንግድ መስኩ እውቀት ላይ የተመሠረተ መረጃ ለመስጠት ኢንስቲትዩቱ በትኩረት ይሰራል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ እና የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ስምምነቱን የፈረሙ ሲሆን፤ የጥናትና ምርምር ሥራው የንግድ ሥርዓትን የማዘመን፣ ግልጽ፣ ተደራሽና ፍትሐዊ ውድድር የማስፈን ተልዕኮን ለማሳካት አጋዥ እንደሆነ ተገልጿል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ‹‹መስረቅ ክልክል ነው›› ይባላል?

**ዋስልኝ አየለ**

መቼም በመሠልጠን ጉዳይ ላይ የጻፍኩት ትዝብት ቢቆጠር ሌሎች ትዝብቶች ሁሉ ተደምረው አይደርሱበትም፡፡ በእርግጥ የአንዲት አገር ዕድገትም የማኅበረሰብ ዕድገት ነው፤ የማኅበረሰብ ዕድገት ደግሞ የአስተሳሰብ ልዕልና ሲኖር ነው፡፡ አንዳንድ ነገሮችን ባየሁ ቁጥር ረዘም ላሉ ደቂቃዎች ስለሀገሬ ሁኔታ አስባለሁ፡፡ ለምንድነው በዚህ ልክ ወደኋላ የቀረነው? የሚለው ነገር አሁንም ጥያቄ ሊሆንብን ይገባል፡፡

ከትናንት ወዲያ ጠዋት (ሰኞ) በአንድ ትልቅ የፌዴራል መሥሪያ ቤት መፀዳጃ ቤት ውስጥ የእጅ መታጠቢያው መስታወት ሥር ‹‹እባክዎ የእጅ ሳሙና ቀንሰው አይውሰዱ!›› የሚል ማሳሰቢያ አየሁ፡፡ የተማረሩ የጽዳት ሠራተኞች ይመስሉኛል የለጠፉት። የተቋሙ አመራሮችም ሆኑ ፅዳቶች ይህን ከማለት ውጭ ምንም አማራጭ የላቸውም፤ ወደው አይደለም ለማለት ነው፤ ሁኔታው አስገድዷቸው ነው። የሚሰርቅ ሰው ስላለ ነው፡፡

እንግዲህ አስቡት የኋላቀርነታችንን ደረጃ! ‹‹አትስረቁ›› ተብሎ መነገር ነበረበት? መስረቅ ክልክል መሆኑ በማሳሰቢያ መጻፍ ነበረበት? ይህን ለማወቅ የትኛውም የትምህርት ደረጃ ይቅርና ዝም ብሎ ሰው መሆን ብቻውን አይበቃም ነበር?

እንዲህ አይነት ሰው በማሳሰቢያም አይመለስም። መቼም የሚሰርቀው ረስቶት አይሆንም፤ አስቦበት ነው፡፡ እንዲህ አይነት የተበላሸ ሥነ ምግባር ያለው ሰው ደግሞ ማሳሰቢያም አይመልሰውም፤ ምክንያቱም ማሰቢያ የለውም፡፡ ማሳሰቢያ የሚደረገው ማሰብ ለሚችል ሰው ነው፡፡ ማሳሰቢያ የሚደረገው የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ነገሮችን ለመለየት ነው እንጂ ጤነኛ ሰው በመሆን ብቻ ሊታወቁ ለሚገባቸው ነገሮች አልነበረም፡፡

ለምሳሌ ‹‹የሴቶች መጸዳጃ ቤት፣ የወንዶች መጸዳጃ ቤት›› ተብሎ የሚጻፈው ወይም ምልክት የሚደረገው የውጭ ሰው (እንግዳ) ማወቅ ስለማይችል ነው፡፡ ወደ አንድ ተቋም ወይም ሆቴል ወይም ሌላ የአገልግሎት ቦታ ስንሄድ ጽሑፍ ወይም የሴትና የወንድ መሆኑን የሚለይ ምስል ከሌለው የሴትና የወንድ መፀዳጃ ቤት ለይተን ልናውቅ አንችልም፡፡ ከመፀዳጃ ቤቱ ውስጥ የእጅ ሳሙና መውሰድ እንደሌለበት ግን ሊነገረው አይገባም፡፡ ውሃ መድፋት እንዳለበት፣ የእጅ መታጠቢያውን ሳይዘጋ መሄድ እንደሌለበት ግን ሊነገረው አይገባም ነበር፡፡ ዳሩ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነና እነዚህን ነገሮች ሁሉ መናገር ግዴታ ሆነ ማለት ነው፤ ብክነት!

በአውሮፓዊቷ አገር ኖርዌይ ለትምህርት የቆየ አንድ ጓደኛዬ የነገረኝ ገጠመኝ ነበር፡፡ የሆነ የኳስ መጫወቻ ሜዳ አለ፡፡ ከአፍሪካ የሄዱ ጥቁሮችም አብረው ይጫወታሉ፡፡ ነጮች በልማዳቸው ኳስ ተጫውተው እንደጨረሱ ኳሱን ይዘው አይሄዱም፤ እዚያው ነው የሚቀመጠው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የአንዲት አፍሪካዊት አገር ሰው ወደ ሀገሩ መመለሻ ጊዜው ሲደርስ ኳሷን ይዞ ሄደ፤ ‹‹ለምን?›› ሲባል ‹‹ለልጆቼ መጫወቻ›› ብሎ መለሰ፡፡

አስቡት እንግዲህ ኳስን ያህል ተራ ነገር ከአውሮፓ ሰርቆ ወደ አፍሪካ ሲያመጣ፡፡ ‹‹ለካ ከእኛም አገር የባሰ አለ!›› ብለን ተገረምን አለ ያ ጓደኛዬ፡፡ በነገራችን ላይ ኢትዮጵያዊ ውጭ አገር በጣም ኩሩ ነው፡፡ ቢያንስ የአገሩን ገመና አያሳይም! ግን ጥቁር ነውና ‹‹ከኑግ ጋር ያለሽ መጭ አብረሽ ተወቀጭ›› እንደሚባለው›› አብሮ መታማቱ አይቀርም፡፡

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ነጮች ቢንቁን፣ እንደ እንስሳት ቢቆጥሩን፣ ‹‹ያልሠለጠኑ ኋላቀሮች›› እያሉ ቢሰድቡን ይፈረድባቸዋል? ጥቁር ሲሰደብ ያንጨረጭረናል፣ ደማችን ይፈላል፡፡ ያ ወኔ እና እልህ ግን የምንሰደብበት ምክንያት ላይም ጠንካራ ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት የተበላሸ ሥነ ምግባር ሲያጋጥመን ልክ ነጭ እንደሰደበን ሁሉ ለዚህም ልንቆጣ ይገባል፤ ምክንያቱም ያ ነጭ የሰደበን በዚህ ምክንያት ነው፡፡

‹‹የሥልጣኔ ባለቤት ነን፣ ቅኝ ያልተገዛን ኩሩ ሕዝቦች ነን›› እያሉ መፎከር ብቻውን ለዛሬ ኩራት አይሆንም፡፡ አዎ! የሥልጣኔ ባለቤቶች ነን፤ ዳሩ ግን በዚያው ልክ ደግሞ የብዙ ብልሹ ሥነ ምግባሮች ባለቤትም ሆነናል፡፡ ‹‹ውሃ ይድፉ›› ተብሎ ማሳሰቢያ የሚጻፍበት ተቋም ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ዲግሪ እና ማስተርስ የትምህርት ደረጃ የደራረቡ ናቸው። የዓለምን የሥልጣኔ ደረጃ ለማወቅ ቅርብ ናቸው። ዳሩ ግን እንደ ሕጻን ስለግል እና አካባቢ ንፅሕና እየተነገራቸው ነው፡፡

ስለራሳችን ገመና ላውራ ብዬ እንጂ ሌሎች ከዚህ የባሱ ሀገራት እንዳሉ የብዙ ሰዎችን ገጠመኞች ሰምቻለሁ፣ አንብቤያለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ኩራት የሆነው አየር መንገዳችን አየር ማረፊያ በሄድኩ ቁጥር፤ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስለአንዲት ሀገር ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ የጻፉት ትዝ ይለኛል። በዚያች ሀገር አየር ማረፊያ ውስጥ ያለው መፀዳጃ ቤት በእጅ እንኳን ለመንካት በሚቀፍ ቆርቆሮ መሳይ ነገር መጥፎ ሽታ የፈጠረ ውሃ ነው፡፡ ይህን እንግዲህ እዚያ ቦታ የደረሰ የዓለም ዜጋ ሁሉ ያየዋል፡፡

ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ስትገቡ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ መሆናችሁ ሁሉ ይረሳችኋል፤ ለዚያውም እኔ ያየሁት የሀገር ውስጥ በረራውን ነው፡፡ በሌሊትም በቀንም አይቸዋለሁ፡፡ 24 ሰዓት የሚሠሩ (ለዚያውም ከትህትና ጋር) የጽዳት ሠራተኞች ናቸው ያሉት፡፡ ወደ አፍንጫ የሚመጣው ሽታ ‹‹ሽንት ቤት ነው ሳሎን ነው ያለሁት!›› ያሰኛል። መጸዳጃ ቤት መሆኑን የምታውቁት ሲንኩን በማየት ብቻ ነው፡፡ እንደዚህም ማድረግ ይቻላል ለማለት ነው።

መቼም ሁሉም ተቋም የ24 ሰዓት የጽዳት ሠራተኛ ሊቀጥር አይችልም፡፡ ለተጠቃሚም ምቾት አይሰጥም፡፡ ዋናው ነገር ዜጋው ሲሠለጥን እና የኔነት ስሜት ሲሰማው ነው፡፡ ያ ካልሆነ የ24 ሰዓት የጽዳት ሠራተኛ ቢቀጠርም መበላሸቱ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም የሚያበላሸው አንድ ሰው ነው፡፡ ይህን ሁሉ ብልሹ ነገር የምናየውም በጥቂት ምግባረ ብልሹ ሰዎች ነው፡፡

ጽዳት ላይ ያተኮርኩት የጤና ነገር ስለሆነ ነው እንጂ በብዙ የአገልግሎት ማግኛ ቦታዎች ላይ ብዙ አይነት ችግር አለ፡፡ ለምሳሌ፤ ብዙ ጊዜ ከሚገርሙኝ ነገሮች አንዱ የአሽከርካሪዎች በክላክስ መጫወት ነው፡፡ ከፊቱ ያለ ተሽከርካሪ በትራፊክ መብራት ቆሞ ከኋላ ያለው ያለማቋረጥ ክላክስ ያንባርቃል፡፡ መንገድ ዳር ቆመው ከአስፋልት ማዶ ካለ ካፌ አስተናጋጅ የሚጠሩት በክላክስ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሰው እየረበሹ ነው፡፡

በአጠቃላይ፤ ምራላዊ እና ጤነኛ ሰው በመሆን ብቻ ልናውቃቸው የሚገቡ ነገሮችን ‹‹አታድርጉ›› የሚል ማሳሰቢያ እየተሰጠን ነው፡፡ ማሳሰቢያ የሚደረገው የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮችን ለመለየት ነበር፡፡ የሥልጣኔ ደረጃችን ግን ‹‹መስረቅ ክልክል ነው›› የሚል ማሳሰቢያም እንዲኖረን እያደረገ ነውና የሥልጣኔ ባለቤትነታችንን በተግባር እናሳይ!

# ዓለም አቀፍ

## የግብፁ ፕሬዚዳንት አል ሲሲ ለሦስተኛ ጊዜ አሸነፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታህ አል ሲሲ 89 ነጥብ 6 በመቶ ድምፅ በማግኘት ለሦስተኛ ጊዜ ማሸነፋቸውን የሀገሪቱ የምርጫ ኮሚሽን አስታወቀ። አል ሲሲ በሦስተኛ የሥልጣን ዘመናቸውም ለቀጣዩ ስድስት ዓመታት ሀገሪቷን የሚመሩ ይሆናል።

የቀድሞው የጦር አዛዥ አል ሲሲ ብዙም ዕውቅና የሌላቸውን ሦስት የፕሬዚዳንት ዕጩዎቻቸውን በሰፊ ድምጽ ማሸነፋቸው ተነግሯል። በዚህ ምርጫ አል ሲሲን በሁለተኛነት የተከተሉት ዕጩ ያገኙት ድምፅ 4ነጥብ 5 በመቶ ብቻ ነው።

የተቃዋሚው መሪ አሕመድዞ ታንታውይ በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት ዛቻ እንዲሁም በቡድናቸው ላይ ጥቃት ተሰንዝሮባቸዋል በሚልም ከወራት በፊት ከምርጫው ራሳቸውን አግልለው ነበር።

የግብፅ የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል እንዲሁም የጋዛ ጦርነት የምርጫው ቁልፍ ጉዳዮች ነበሩ።

የ69 ዓመቱ ሲሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥልጣንን የተቆናጠጡት በአውሮፓውያኑ 2014 ሲሆን ከዓመት በፊትም የሀገሪቱን ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲን ከሥልጣን ያስወገደውን መፈንቅለ መንግሥትም መርተዋል።

ፕሬዚዳንት ሲሲ በቀጣዩ በተደረገው 2018 ምርጫም በድጋሚ ማሸነፍ ችለዋል። አሁን በተደረገው ምርጫ ያሸነፉት አል ሲሲ ሀገሪቱን እስከ አውሮፖውያኑ 2030 ድረስ እንዲመሩ ያስችላቸዋል፡፡

በእርሳቸው የሥልጣን ዘመን ሀገሪቷ ለትላልቅ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ አፍስሳለች። ሰፋፊ መንገዶች ተዘርግተዋል፣ ረጃጅም ድልድዮች ተገንብተዋል እንዲሁም በካይሮ አቅራቢያ ቢሊዮኖች ዶላር የፈጀ አዲስ መዲናም ተቋቁሟል።

ይህም የሀገሪቱን አብዛኛውን ሀብት በማሟጠጥ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ እዳ በመዝፈቅ ምጣኔ ሀብቷን አሽመድምዶታል በማለትም ይተቿቸዋል።

በዋጋ ግሽበት እየተፈተነች ያለችው ግብፅ የመገበያያ ገንዘቧ ፓውንድም እያሽቆለቆለ ይገኛል።

የግብፅ ምጣኔ ሀብት ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኛ ሲሆን መሠረታዊ የሸቀጥ ፍጆታዎች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ንሯል፤ የውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያም ተስፋፍቷል።

ይፋዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከግብፅ 100 ሚሊዮን ሕዝብ 30 በመቶው የሚጠጋው ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ነው። ከምጣኔ ሀብት ተግዳሮት በተጨማሪ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች የሀገሪቱ የፖለቲካ ምሕዳር የጠበበ ነው ሲሉ ይተቻሉ።

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ሀገሪቷ የጣለቻቸው ጥብቅ የፀጥታ ገደቦች የመብት ጥሰቶችን ለመመዝገብ አስቸጋሪ አድርጎታል ይላሉ። የግብፅ ባለሥልጣናት ግን ክሱን ያስተባብላሉ። ዘገባው የቢቢሲ ነው፡፡

## ዩክሬን የውጭ ድጋፍ በመቀነሱ ወታደራዊ ዘመቻዎችን ለማቋረጥ መገደዷን አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ከሩስያ ጋር ጦርነት ላይ ያለችው ዩክሬን ከሌሎች ሀገራት የሚደረግላት ድጋፍ በመቀነሱ ምክንያት የተወሰኑ ወታደራዊ ዘመቻዎችን ለመቀነስ እየተገደደች መሆኑን አስታወቀች።

ቢቢሲ እንደዘገበው፤ የሀገሪቱ ወታደሮች “በሁሉም የውጊያ ግንባር” የተተኳሽ ጥይት እጥረት ስላጋጠማቸው “ትልቅ ችግር” እየተፈጠረ መሆኑን የዩክሬን ከፍተኛ ጀኔራል የሆኑት አሌክሳንደር ተርናቭስኪ ተናግረዋል።

ዩክሬን ይህ ችግር ያጋጠማት ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ኅብረት በድጋፍ ልታገኝ የነበረው የቢሊዮኖች ዶላር ድጋፍ በፖለቲካዊ አለመግባባት ምክንያት ተይዞ በመቆየቱ ነው።

ዩክሬን በምዕራባውያን ሀገራት እርዳታ የራሷን ጥይት በማምረት ክምችቷን ከፍ ለማድረግ እቅድ እንዳላት አስታውቃለች። ነገር ግን ከሩስያ ጋር የምታደርገው ጦርነት በከፍተኛ ደረጃ የተመሠረተው ከምዕራባውያኑ ሀገራት በሚቀርብላት የጦር መሣሪያዎች ላይ ነው። በተለይም የረጅም ርቀት ሚሳኤሎች እና የአየር መከላከያ ሥርዓት አቅርቦት የምታገኘው ከእነዚሁ ሀገራት ነው።

ዩክሬን በተለይም ከሶቪየት ኅብረት ጊዜ አንስቶ አገልግሎት ላይ እየዋሉ ላሉት ከባድ የጦር መሣሪያዎች የሚሆን ተተኳሽ እጥረት መኖሩን ጀኔራል ተርናቭስኪ ለሮይተርስ የዜና ወኪል ተናግረዋል።

“ካለን ፍላጎት አንጻር ያለን የተተኳሽ ብዛት በቂ አይደለም” ያሉት ጀኔራሉ፤ “በዚህም የተነሳ ያሉንን መልሰን እያከፋፈልን ነው። ልንተገብር ላሰብናቸው ተግባራት [ጥይት] ማቅረብ ስላለብን ያስቀመጥናቸውን እቅዶች መልሰን እየከለስን እና መጠናቸው እንዲቀንስ እያደረግ ነው” ሲሉ ያጋጠመውን ችግር ገልጸዋል።

የውጭ ሀገራት የሚያደርጉት ወታደራዊ ድጋፍ መቀነሱ በውጊያ ሜዳ ላይ ተፅዕኖ እያደረሰ መሆኑን እና የውጊያ ስልት ለውጥ እንዲደረግ እያስገደደ መሆኑንም ጀኔራሉ አክለዋል።

አሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት የሚያደርጉት ድጋፍ ላይ እቀባ አድርገዋል። በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ የሚገኙ ሪፐብሊካን ለዩክሬን ሊሰጥ ታስቦ የነበረን የ60 ቢሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ አግደዋል።

ባለፈው ሳምንት ደግሞ የአውሮፓ ኅብረት ለሀገሪቱ ሊሰጥ የነበረውን 55 ቢሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ሀንጋሪ እንዲታገድ አድርጋዋለች። ይሁንና የኅብረቱ አመራሮች ዩክሬን ያለ ምንም ድጋፍ እንደማትቀር ገልጸዋል።

የአውሮፓ ኅብረት እስከ መጪው መጋቢት ወር ድረስ አንድ ሚሊዮን ተተኳሽ ጥይት ለማቅረብ ቃል ቢገባም እስካሁን ማቅረብ የቻለው 480 ሺህ ያህሉን ብቻ ሲሆን ከዚህ ውስጥም የተወሰነው በሂደት ላይ ነው።

አሜሪካ ሁለት ሚሊዮን ባለ 55 ሚሊ ሜትር ጥይት ለዩክሬን ማቅረብ ብትችልም አሁን ላይ የምታቀርበው የተተኳሽ አይነት ላይ ለውጥ አድርጋለች።

ዩክሬን ያላት የተተኳሽ ፍላጎት አጋሮቿ የሆኑ ሀገራት ማቅረብ ከሚችሉት አቅም በላይ ነው። እንደ ኢስቶኒያ መከላከያ ሚኒስቴር ገለጻ ዩክሬን በሩስያ ላይ የበላይነቱን ለመቀናጀት በየወሩ ቢያንስ 200 ሺህ የከባድ መሳሪያ ተተኳሾች ያስፈልጓታል።

ሩስያ፤ ዩክሬን ያጋጠማትን የወታደራዊ ድጋፍ እጥረት እንደ ጥሩ እድል በመውሰድ ምጣኔ ሀብቷን ወደ ጦርነቱ በማዞር በተራዘመ ጦርነት ለማሸነፍ ልትሠራ ትችላለች የሚል ስጋት ተፈጥሯል።

ባለፈው ሳምንት የሩስያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጦርነቱ የሚጠናቀቀው ሩስያ “ግቧን ስታሳካ ነው” ብለው ነበር።

# አስታራቂ ሃሳቦች - የሀገር ማጽኛ ካስማ ናቸው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

"አስታራቂዎች ብጹዕን ናቸው" ይላል ታላቁ መጽሐፍ:: ማስታረቅም ሆነ መታረቅ ለብጹዕነት የሚያበቃ የክብር አክሊል ከሆነ፤ ማስታረቅና መታረቅ ለምን አቃተን? ወደሚል ጥያቄ እመጣለሁ:: የትኛውም ችግር አስታራቂ ሃሳብ ካገኘ ወደፍቅር የማይመጣበት ምንም ምክንያት የለም:: ችግሮቻችንን ከዚህ አንጻር ስንቃኛቸው አስታራቂ ነው ያጣነው ወይስ አስታራቂ ሃሳብ ነው የሌለን? ወደሚል ይመሩናል:: አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሁለቱንም ያጣን ነን:: ሁለቱንም ማጣት ደግሞ ጉዳቱ ምን ያክል እንደሆነ መረዳት አይከብድም::

ብሔራዊ ምክክር የአስታራቂነትን ሚና በመውሰድ ሃሳብ ተኮር በሆነ ሕዝባዊ መድረክ መጥቷል:: ይሄ እድል ላጣነውና እያጣነው ላለው ፍቅርና አንድነት እንደ መልካም አጋጣሚ የሚወሰድ ብቻ ሳይሆን ዳግም የምንተቃቀፍበት የእርቅና የይቅርታ መድረክም ጭምር ነው። ስለሆነም ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንን እንደ አስታራቂ በመውሰድ የመታረቂያ ሃሳቦችን ደግሞ ከእያንዳንዳችን በማዋጣት ከምንምነት ሁሉም ወዳለው ማንነት መሸጋገር ይቻላል::

የተለያዩ የዓለም ሀገራት ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በእንዲህ ዓይነት መንገድ ነው የፈቱት:: ለአብነት ደቡብ አፍሪካንና ሩዋንዳን ብንወስድ ለእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ጥሩ አርአያ የሚሆኑ አፍሪካዊ ሀገራት ናቸው:: በዚህ ሕዝባዊ ተሳትፎ በኩል ነው አሁን ላላቸው ሀገራዊ ቁመና የበቁት:: በርግጥ በእድሉ ያልተጠቀሙ አንዳንድ ሀገራትም አሉ:: መድረክ አዘጋጅቶ ከመወያየት ባለፈ ይሄ ነው የሚባል ቁም ነገር ያልሰሩ::

የእኛ ሀገራዊ ምክክር ግን ከዚህ የተለየ ነው። በልምድና በተሞክሮ፣ በሕዝባዊ ውይይት ሀገር ከለወጡ የአፍሪካና የአውሮፓ ሀገራት ተሞክሮ ተወስዶ የተጀመረ ነው:: ልክ እንደዚህ ሁሉ ከዚህ በፊት ሳንጠቀምባቸው ባለፉን የሀገራዊ ምክክር እድሎች ተምረን ለለውጥና ለተሐድሶ እንቅስቃሴ የጀመረ ነው:: ስለሆነም አዋጪነቱ ከፍ ያለ ነው:: በሄደባቸው ዓመታትን በወሰደ የዝግጅትና የቅድመ ሁኔታ እንቅስቃሴ አላማውን እንደሚመታ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው:: አሁናዊ ቁመናውን ብንፈትሽ እንኳን የምክክሩ የመጨረሻ ምዕራፍ በሆነውና ወደ ተግባር በሚወስደው የክዋኔ አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ተችሏል::

በአስራ አንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለምክክሩ የተሳታፊ ልየታና የአጀንዳ መረጣ መነሻ ሃሳቦችን የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነ የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለ መጠይቅ አረጋግጠዋል:: ኃላፊነት እንዳለበት ባለአደራ ኮሚሽን ሁሉንም ነገር በጥንቃቄና በኃላፊነት ይዞ እየተጓዘ እንደሚገኝም በተለያየ ጊዜ ከሰማናቸው የኮሚሽኑ መግለጫዎች ለማወቅ ችለናል::

ታዲያ ኮሚሽነሩ በቃለ ምልልሳቸው ወቅት እንዳሉት፤ በሀገሪቱ ከሚገኙ አስራ ሶስት ክልሎች በአስራ አንዱ ላይ የተሳታፊ ልየታና የመወያያ አጀንዳዎችን የማሰባሰብ ሂደት ጨርሶ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ተሸጋግሯል:: በኦሮሚያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በሱማሌ ክልል የተባባሪዎችን ሥልጠና ጨርሶ ወደሌሎች ክልሎች በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን፣ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ አባገዳዎችን፣ ሀዳ ሲንቄዎችን፣ ከእድር የተወጣጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን ያሳተፈው የተባባሪዎች ሥልጠና በዝግጅትና በቅድመ ሁኔታ የተሳካለት እንደነበር ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) ገልጸዋል::

በአማራና በትግራይ ክልል ተመሳሳይ ሥራ ሊሰራ ዝግጅት ያለቀ ሲሆን፤ በተለይ ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን፣ ከሲቪክ ማህበራትና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ጥሩ ሥራ እንደሚሰራ አያይዘው ተናግረዋል:: ከዋናው ሀገራዊ ምክክር በፊት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ክልላዊ ሕዝባዊ ምክክር እንደሚደረግ የተጠቆመ ሲሆን ከዞን፣ ወረዳና ቀበሌ የተመረጡ ተሳታፊዎች በክልል ደረጃ ቅድመ ምክክር እንደሚያደርጉ በኮሚሽነሩ በኩል ተገልጿል። ከዚህ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ በውጭ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች በዚህ ምክክር ላይ የበኩላቸውን እንደሚያደርጉ ተጠቁሟል::

> **በሀገራዊ ምክክር መድረክ ላይ ስንቀርብ ተሟግቶ ለማሸነፍ፣ ተከራክሮ ለመርታት ሳይሆን፤ ተወያይቶ ለመግባባት እና ወደእርቅ ለመሄድ እንደሆነ መረዳቱ አላማችንን ለመጨበጥ ወሳኝ ነው**

በያዝነው በ2016 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው ሕዝባዊ የእርቅና የተግባቦት መንገድ እንደ አጀማመሩ ጥሩ ውጤቶችን ለሀገርና ሕዝብ ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል:: በትላንት በዛሬ የፖለቲካ ዥዋዡዌ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ለምትል፣ ባልሻረ እና ሊሽር ባላለ ቁስል እዬዬ ለምትል ሀገር ይሄን ዓይነቱ ነጻና ገለልተኛ መድረክ መፍትሔ ስለመሆኑ ብዙዎች መስክረዋል::

የነበሩና ያሉ ወደፊትም የሚኖሩ አንድነትንና አብሮነትን የሚያወይቡ ችግሮች በጦርነት ሳይሆን በምክክር እንደሚፈቱ ለትውልዱ አጽንኦት ከመስጠት ባለፈ የተለማመድናቸውን እልፍ የኃይል ልምምዶች ያስቀራል ተብሎ ይታሰባል:: ከጦርነት በፊት ውይይትና እርቅ አልሆን ብሎን ከብዙ ዋጋ መክፈል በኋላ እየተጨባበጥን ቅደም ተከተሉን ባልጠበቀ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ፊተኝነትን ተነጥቀን ኋለኞች ሆነናል::

ባስታራቂነቱና በይቅር ባይነቱ ታሪክ የጻፈ የሰላምና የፍቅር አለቃ ሕዝብ በአጉል ትርክት ሰላምና አንድነት አጥቶ ላልኖረበት ዘመን እዳ ሲከፍል ሰንብቷል:: በወንድማማች መሀከል ጠብን በሚዘሩ ጥቂቶች ብዙኃኑ ተፈራርቶ የጎሪጥ እየተያየ ኢትዮጵያዊነትን ፈርቶ ሸሽቶ ቆሟል::

ከሌማቱ እያነሳ፣ ከገንቦው እየቀዳ ከብላና ጠጣ በቀር ጉርብትና የሌለው ሕዝብ ዛሬ እንደ አይጥና ድመት ካብ ለካብ እየተያየ የፍቅር ወደቡን በስጋት ቀይሯል:: ለጥቂት ትርፍ ታሪክ አዛንፈው፣ በሀሰት ስብከት፣ ትውልዱን ደም ለማቀባባት ራሳቸውን ፊተኛ ያደረጉ እኩያን ጥንተ ፍቅራችንን ነጥቀውናል:: ከኢትዮጵያዊነት ሌላ ምልክት የሌለን በኩረ ነፍሶች በብሔር ስም ሌላ ምልክት አድርገውናል:: ኢትዮጵያ የሚለውን አፍ የፈታንበትን የልጅነት እውቀታችንን በዘረኝነት ለውጠው ተወናብደው አወናብደውናል::

መዳኛችን ምንድነው? መዳኛችን ስክነት ነው። ሰክነንና ረግተን በኢትዮጵያዊነታችን መሀል ምን እየተካሄደ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል:: ከዚህ መረዳት በኋላ ስናደርገው የነበረውና አሁንም እያደረግነው ያለው ነገር ልክ እንዳይደለ መረዳት ላይ እንደርሳለን:: ከዚህ ንቃት በኋላ ወደነበርንበት የከፍታ ማማ በሚወስደን የመፍትሔ ሃሳብ ላይ እናተኩራለን::

መፍትሔው ደግሞ ስለአንድነትና አብሮነት የሚከፈል የጋራ መስዋት ይሆናል:: ይሄውም ምክክርና ውይይት እርቅና ተግባቦት ሆኖ ይገለጣል:: መጀመሪያ ስንነሳ በስክነት ነበር:: ቀጥሎ ምን እንደነበርንና አሁንስ ምን እንደሆንን ድሮና ዘንድሮን ወደ መረዳት መጣን:: ቀጥለን እያደረግነው ስላለው ነገር ማሰብ ጀመርን:: ቀጥለን የመፍትሔ ሃሳብ ላይ አተኮርን:: በስተመጨረሻም ኢትዮጵያዊነትን በሚመልስ እርቅና ምክክር ላይ አረፍን::

እናም በስክነት ተነስተን በእርቅ ለመቋጨት ተነሳን:: ከዚህ እውነታ በመነሳት እንደ ሀገር ምን እንደጎደለን ማወቅ እንችላለን:: ስክነት የለንም። በኃይል ካልሆነ ሰክነንና ረግተን መፍትሔ የሰጠንበት ጉዳይ እምብዛም ነው:: ከየትም፣ እንዴትም ይነሱ መከራዎቻችን የእኛን ትዕግስት ማጣት ተጠቅመው ነው የልብ ልብ ያገኙት። የመከራዎቻችን አቀጣጣዮች በመሆን፣ እኛው በእኛው ላይ ጨክነን ብዙ ዋጋዎችን ከፍለናል:: ለዚህም ነው መከራ እንዲበቃን ስክነት የታከለበት አእምሮና ልብ ያስፈልገናል::

ስክነት የምንም ነገር መነሻ ነው:: ክፉን የሚያራራ፣ ኃይለኛውን የሚያረጋጋ:: ስለዚህ በኃይልና በእልህ ተሞልተን ርምጃ ከመውሰዳችን በፊት በስክነት ሁሉንም መቃኘት ዋጋ ከመክፈል የሚታደግ ብልህነት ነው:: እንደ ሀገር ይሄ ብልሃት ያስፈልገናል:: በፖለቲካውም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ስክነት ያለበት ብልሃት እጅግ አትራፊ ነው::

በሀገራዊ ምክክር መድረክ ላይ ስንቀርብ ተሟግቶ ለማሸነፍ፣ ተከራክሮ ለመርታት ሳይሆን፤ ተወያይቶ ለመግባባት እና ወደእርቅ ለመሄድ እንደሆነ መረዳቱ አላማችንን ለመጨበጥ ወሳኝ ነው:: ዛሬኮ እና መቼና እንዴት በማን እንደተፈጠሩ በማናውቃቸው ትርክት ውስጥ ነን:: እኚህ ሁሉ ስክነት ይሻሉ:: ቢያንስ ከየት መጡ? ማን አመጣቸው? ለምን መጡ? የሚለውን መሠረታዊ የእርቅ ጥያቄ ለመመለስ ይረዱናል:: እኚህ ጥያቄዎች እንደ ሀገር ወደተግባቦት ለመሄድ ወሳኝ ናቸው:: ወሳኝነታቸው የሚረጋገጠው ደግሞ ሰክነን ስንናገር፣ ሰክነን ስናደምጥ እና ሰክነን ስንግባባ ነው::

አስታራቂ ምክሮች የሀገር ምሰሶዎች፣ የትውልድ ካስማዎች ናቸው:: በጎ አንደበቶች የፍቅርና የይቅርታ አስኳል ናቸው:: በወሬ እንደፈረስን ሁሉ መጽኚያችንም አስታራቂ ሃሳብ ነው:: በትርክት እንደተለያየን ሁሉ መተቃቀፊያችንም ስክነት ነው። ያልበላንን ከማከክ ወጥተን አልድን ላለን ቁስላችን መፍትሔ ማምጣቱ ላይ ማተኮር ነው ዘላቂ ሰላምን የሚሰጠን:: ከይዋጣልን ወጥተን እንዴት በውይይትና በድርድር አሸናፊ መሆን እንደሚቻል ማወቁ ነው በትላንት እንዳንዳከር በዛሬ እንዳናፍር የተሐድሶ አቅጣጫን የሚሰጠን::

ብሔራዊ ምክክር እንደ ስሙ ሀገራዊ ተግባቦትን የሚፈጥር ከሕዝቦች ለሕዝቦች ጽንሰ ሃሳብ ነው:: ከሕዝብ የሚነሱ ማናቸውም ቅሬታዎች እንዲህ ባለው መድረክ ፊት መፍትሔ የሚሰጣቸው ናቸው:: ከላይ እንዳልኩት የትኛውም ውይይት ፍሬ የሚያፈራው አስቀድሞ ለእርቅ በተሰናዳ አእምሮ በኩል ነው:: ለውይይት ስንቀመጥ ለማሸነፍ ሳይሆን ለመሸነፍ፣ ለመርታት ሳይሆን ለመረታት ነው:: ምክንያቱም የምንፈልገው የሰላምና የአብሮነት ትንሳኤ ያለው በመሸነፍ ውስጥ ስለሆነ::

ነገር ግን በማሸነፍ ስለመጣን የመሸነፍን ዋጋ አላወቅነውም:: ትላልቅ ድሎች ያሉት በመሸነፍ ውስጥ እንደሆነ የገባቸው ጥቂቶች ናቸው:: እኛም ስለፍቅር ስንል፣ ተዋዶና ተከባብሮ ስለኖረ ሕዝብ ስንል ስለአብሮነት መሸነፍን ካልመረጥን በማሸነፍ ፖለቲካ እና የኃይል ልምምድ አርነት መውጣት አይቻለንም:: ትላንትን ረስቶ፣ ዛሬን ተስማምቶ ነገን ተስፋ አድርጎ ለመኖር ስለአብሮነታችን ብዙ የቤት ሥራዎች አሉብን::

በፖለቲካ እና በአጉል ትርክት ቁስለኛ ከሆንን ዘለግ ያለ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ቁስሎቻችን ከመዳን ይልቅ ጥዝጣዜን እየፈጠሩ እንደ ሀገር ህበሳን፣ እንደ ትውልድ ደግሞ ጥላቻን አልብሰውናል:: ቁስሎቻችንን ከማዳን ይልቅ እንዳይድኑ እሽሩሩ እያልን እንደመጻጉ ድውዮች ሆነን ይሄው አጎንብሰናል:: ካጎነበስንበት ቀና ማለትን ገንዘባችን እናድርግ። ባልገባንና ባላወቅነው ሁናቴ እያዳለጡ የጣሉን የራስ ወዳድነት ማቆች ከላያችን ላይ ተቀደው እንዲወድቁ መሸነፍ ያለበት፣ ፍቅርን ፊተኛ ያደረገ የምክክር እና የእርቅ ፍኖት እንደሚያስፈልገን ስጠቁም በርግጠኝነት ነው::

ሀገራችን እንደ ሀገር አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ተሸልማ፣ በህብረ ብሔራዊነት ቆንጆታ የነጻነት እና የሉዓላዊነት ፋና ወጊ የሆነችው በምክረ ሃሳብ ነው:: ሕዝባችን በአብሮነት እና በመደማመጥ የጀገነው አንድም አክብሮ ሁለትም ተከብሮ ነው:: እነዛ ፊተኝነትን ያጎናጸፉን የአብሮነት ቀለሞቻችን ዳግም አብበው እንዲያደምቁን የሃሳብ መዋጮ ያስፈልገናል:: አንተም ተው አንተም ተው የሚሉ የእርቅ ሃሳብ:: በመሸነፍ ውስጥ ማሸነፍ እንዳለ የሚሰብኩ ብሩካን አንደበቶች ያሹናል::

ስለዚህም ሃሳብ እናዋጣ:: ሀገራችንን በሃሳብ ማግረን በፍቅር ካላጸናናት ከብሔር ቡዳኔ አንወጣም:: ገርተውና አቃንተው የሚያስተቃቅፉ አስታራቂ ሃሳቦች ያስፈልጉናል:: የምንናገረውን የሚያደምጥ ብዙ ትውልድ አለ:: የሰማውን የሚናገር እንደዚሁ ሌላ ትውልድ አለ:: ሀገር የቅብብሎሽ ሀብት ናት:: ከዛሬ ወደ ነገ ፍቅርን እንጂ ጥላቻን ይዘን እንዳንሄድ በፍቅር የሻረ ትውልድ መገንባት ኢትዮጵያን ከምንወድ ከሁላችን የሚጠበቅ ተግባር ነው::


በእንዲህ ካልሆነ ቁስሎቻችንን አናሽራ ቸውም:: በእንዲህ ካልሆነ ጥዝጣዜዎቻችንን አናክማቸውም:: ብሔራዊ ምክክር ኢትዮጵ ያዊነትን ወደነበረበት የተባበረ ሕብረት ለመመለስና የሕዝቦችን ወንድማማችነት ለማረጋገጥ ላለፉት ዓመታት ሚናውን በመወጣት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ቆሟል:: ከእኛም የሚዋጣ የሃሳብ መዋጮ አለና በጋራ ሃሳብ በቂምና ቁርሾ ከጎበጥንበት አካሄድ ወጥተን በፍቅርና በይቅርታ ለመቅናት እንረባረብ::

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# የሰማዩ አርበኛ ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ

ክብረአብ በላቸው



በኢትዮጵያ ታሪክ እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን፤ስማቸው ከፍ ብሎ የሚነሳ ብዙ ታሪክ የሰሩ ጀግኖች ተፈጥረዋል:: እንዲህ ያሉ ጀግኖች መፍጠር የቻሉ ተቋማትም ስማቸው አብሮ ይነሳል። ከእነዚህ ተቋማት መካከል ባሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ ላይ የ88ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በተለያየ ዝግጅት ያከበረው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አንዱ ሲሆን፤ ጀግኖችን በማፍራት በጉልህ ከሚጠቀሱ ተቋማት መካከልም ቀዳሚ ሆኖ ስሙ ይነሳል።

ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስም ከዚህ ተቋም የወጣ የሀገር ባለውለታ ጀግና ነው:: የሀገርን ዳር ድንበር ለማስጠበቅ በጀግንነት ከተፋለሙ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች መካከል አንዱ ነው።

ጀግናው ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ከአባቱ ከአቶ ጴጥሮስ ሎዳሞ እና ከእናቱ ከወይዘሮ ሸዋዬ አብርሃም በአሁኑ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ ዞን ምስራቅ ባዳዋቾ ወረዳ አንደኛ አምቡርሴ ቀበሌ ሐምሌ 13 ቀን 1943 ዓ.ም ነው የተወለደው::(ፎጊ) በሚል የበረራ ኮድ ስሙ የሚታወቅ የሰማዩ ጀግና ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ለወላጆቹ ሶስተኛ ልጅ ነው።

ከልጅነቱ ጀምሮ በአመለሸጋነቱ ይታወቃል:: ደፋር፣ቁጡ ግን ደግሞ ይቅር ባይና ተግባቢ ባህሪይ መገለጫው ነው:: ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ትምህርትቤት ገብቶ የተከታተለ ሲሆን፤ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በሆሳዕና ከተማ በቀድሞ ራስ አባተ ቦያለው በአሁኑ የካቲት 25/67 ትምህርት ቤት ትምህርቱን ለመከታል በቅቷል:: በትምህርት አቀባበሉም ቢሆን ፣ንቁና ጎበዝ ነበር:: ወታደር የመሆን ዝንባሌም ነበረው::

ኮሎኔል በዛብህ 12ኛ ክፍል ሆኖ ነበር በወቅቱ የኢትጵያ አየር ኃይል ባወጣው ማስታወቂያ የተወዳደረው:: የተሰጠውን ምዘና በብቃት በመወጣት ጥር 26 ቀን 1961 ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ተቀላቀለ::

የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ከተቀላቀለ በኋላ በተቋሙ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በብቃት ተከታትሏል።ከተከታተላቸው የሥልጠና ዘርፎች ውስጥ፡- የስድስት ወር መሠረታዊ የውትድርና ትምህርት(ኮርስ)፣የሰባት ወር መሠረታዊ የበረራ ኮርስ፣የስድስት ወር የመጀመሪያ ደረጃ የበረራ ሥልጠና ኮርስ፣የአውሮፕላን አብራሪነት ዲፕሎማ እንዲሁም ከፍተኛ የተዋጊ አውሮፕላን ሥልጠና ኮርስ በሀገር ውስጥ ሰልጥኗል።

ከሀገር ውጭ በሀገረ አሜሪካ እና በቀድሞ ሶቭየት ህብረት የሚሰጠውን የበረራ ትምህርት ስልጠና ተከታትሎ በብቃት አጠናቋል::በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት በወሰዳቸው የሥልጠና ኮርሶች ባገኘው ዕውቀት እና ክህሎት እንዲሁም ባዳበረው ልምድ በአየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ለረዥም ጊዜ ተዛዋውሮ አገልግሏል::

ኮሎኔል በዛብህ አገልግሎት ከሰጠባቸው የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ በተዋጊ አውሮፕላን አብራሪነት፣ በበረራ አስተማሪነት፣ በስኳድሮን ምክትል አዛዥነት፣በተዋጊ ስኳድሮን የበረራ አስተማሪነት፣ በበረራ ትምህርት ቤት የትምህርት መኮንን በመሆን (በተደራቢነት)፣በበረራ ትምህርት ቤት አዛዥነት በተደራቢ፣በሰሜን አየር ምድብ ጥገና አዛዥነት፣በኤል-39 አውሮፕላን በረራ አስተማሪነት፣ በበረራ ትምህርት ቤት ምክትል አዛዥነት፣በበረራ ማሰልጠኛ ትምህርትቤት የሥርዓተ ትምህርት ደረጃ እና ምዘና ኃላፊነት፣በበረራ ትምህርትቤት የዕቅድና ሥርዓተ ትምህርት ኃላፊነት፣በኤል-39 አውሮፕላን ስኳድሮን አዛዥነት እንዲሁም በምሥራቅ አየር ምድብ አዛዥ ተደራቢ በመሆን የሰራባቸው ቦታዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ::

በአየር መቃወሚያ ተመትቶ አበቃለት ሲባል ከጅጅጋ እስከ ደብረዘይት በሰላም በመብረር ያሳረፈ ፓይለት እንዲሁም ጠላትን እግር በእግር ተከታትሎ የጠላት ተዋጊ ጄት በማጋየት ታሪክ የሰራ፣ የምንግዜም የኢትዮጵያ ጀግና ነው። ከሀገር ሉዓላዊነት የሚቀድም ምንም ነገር የለም የሚል ፅኑ አቋም እንደነበረው የሚነገርለት ኮሎኔል በዛብህ ይህንን አቋሙን በተግባር ኖሮ ማሳየት ችሏል።

**ኮሎኔል በዛብህ በውጊያ ወቅት በኤርትራ ኃይሎች ከተያዘ በኋላ በህይወት አለ ወይስ የለም የሚል ድምዳሜ ላይ እስካሁን አለመደረሱን ቤተሰቦቻቸው ይገልፃሉ**

ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ታላቅ ገድል ከፈፀመባቸው የውጊያ ውሎዎቹ መሃል የሐምሌ 27 ቀን 1969 ዓ.ም በቀዳሚነት ይጠቀሳል:: በዚያ ወቅት ትምክህተኛው የዚያድባሬ መንግሥት በምሥራቅ ኢትዮጵያ ግዙፍ ወታደራዊ ወረራ ፈፅሞ ነበር:: ይህንን ወረራ ለመመከት ከተሰማሩት የአየር ኃይል (አሜሪካ ሰራሽ ኤፍ 5 ኢ) ተዋጊ ጀቶች መሃል አንዱን የያዘው እሱ ነበር::

በወቅቱ በአጋዴን ሐረዋ፣ አይሻ፣ በእነኖሜጢ እና በሌሎችም ቦታዎች የሮኬት ናዳ በማውረድ ወራሪውን የሶማሊያ ጦር ባለበት እንዲገታ ከማድረግ ባሻገር፣ 8 የጠላት ታንኮችን ከእነ ምድብተኛው ረምርሟል። ይህንን ታላቅ ጀግንነት ባስመዘገበ በ10 ሰዓት ልዩነት እንደገና ወደምሥራቅ ጦር ግንባር በመብረር የኢትዮጵያን አየር ኃይል ብቃት ያስመሰከረም ነው።

ጥቅምት 7 ቀን 1970 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሠራዊት በጅጅጋ ካራማራ ላይ ከፍተኛ ትንቅንቅ ላይ ነበር። ያኔ እሱ ከላይ ከሰማይ በሚያወርደው ቦንብ የሶማሊያን ወራሪ ጦር ብትንትኑን ማውጣት ተያያዘ። በዚህ ጊዜ ከጠላት ወገን በተተኮሰ አየር መቃወሚያ የሚቀዝፈው ኤፍ 5 ኢ ተዋጊ ጀት ተመታ:: ይኼኔ እሱ በዥንጥላ ወርዶ ህይወቱን ማትረፍ ነበረበት::

ነገር ግን የሚያበረውንም ጀት ጭምር እንጂ የራሱን ህይወት ብቻ ማትረፍ አልፈቀደም:: እናም የሚያበረውን ጀት በቆራጥነት እየቀዘፈ ወደ ደብረዘይት አየር ማረፊያ ገስግሶ በሰላም አረፈ። የተመታውም ጀት ተጠግኖ እንደገና ለግዳጅ መሰማራት ችሏል።

የጀግናው ኮሎኔል ገድል ይቀጥላል:: በነገሌ ቦረና ግንባር የተሰማራውን የሶማሊያ ጦር የቦንብ ናዳ በማውረድ ጠላትን ብትንትኑን ማውጣቱን ቀጠለ:: ይህ ብቻ አይደለም፤ ሁለት የሶማሊያ ጦር ጀቶችን በአየር ላይ አጋይቶ መጣል ችሏል። የሚገርመው አንዱን የሶማሊያ ጦር ጀት ያጋየው ሶማሊያ ግዛት ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ስለመሆኑ ታሪክ ያስረዳል።

ጥቅምት ወር 1970 ዓ.ም የሶማሊያ ጦር ጀቶች ድሬዳዋ ከተማ ላይ ጥቃት ፈፀሙ:: ይኼኔ ለጥቃቱ የአፀፋ መልስ እንዲሰጡ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊዎች ታዘዙ:: ከታዘዙት ተዋጊዎች መሃል አንዱ የነበረው ኮሎኔል በዛብህ ነበር እናም ጀቱን እየቀዘፈ የአየር ላይ ትርዒት ጭምር በማሳየት ጀግናው ተልቅ ገድል ፈፀመ:: እናም የሶማሊያን ሚግ 21 ተዋጊ ጀት ከነአብራሪው በአየር ላይ አጋይቶ በሰላም ወደ ደብረዘይት ተመለሰ::

ታህሳስ 13 ቀን 1970 ዓ.ም በዛብህ፤ ዩጎ ውጫሌ በሚባል ቦታ ላይ የሚገኘን የሶማሊያ ጦር መሳሪያ ግምጃ ቤት እና መካናይዝድ ክፍለጦር መምሪያ በቦንብ እያጋየ ሳለ ከጠላት ወገን በተተኮሰበት አየር መቃወሚያ ጥይት የሚያበረው አውሮፕላን ሞተር ክፍል ተመታበት:: በዛብህ ጴጥሮስ አውሮፕላኑ ክፉኛ ቢመታም አልተደናገጠም:: የተመታውን አውሮፕላን መልሶ ደብረዘይት ለማሳረፍ ታላቅ ጥረት አደረገ። ሆኖም ጥረቱ አልተሳካም፡ የአውሮፕላኑ ነዳጅ አለቀበት:: በዚህ የተነሳ ደብረዘይትና ሞጆ መሃል በሚገኝ ገላጣ ሜዳ ላይ አውሮፕላኑን አሳርፎ ድርብ ጀግንነቱን አስመሰከረ::

ጀግናው በዛብህ ጴጥሮስ፤ በኢትዮጵያና በሶማሊያ ድንበር ተፈሪ በር በተባለ የጦር መንደር ላይ የሚገኘውን (በጥር ወር 1970) የከባድ መሳሪያ ግምጃ ቤት እና የጠላት ጦርም ድባቅ መታ:: በዚህ ወቅት 5 የጠላት ታንኮችን ከነምድብተኛቸው ደመሰሰ:: ይሁን እንጂ አሁንም ከጠላት በተተኮሰ ፀረ አውሮፕላን ጥይት ተመቶ የሚያበረው አውሮፕላን በእሳት ተያያዘ። ጀግናው ይህም ጥቃት አላሸበረውም:: እሳቱን በመከላከያ በማጥፋት ወደመጣበት ተመለሰ:: አሁን ግን ደብረዘይት መድረስ አልቻለም:: አውሮፕላኑን ድሬዳዋ አየር ማረፊያ አሳረፈው:: አውሮፕላኑም ተጠግኖ እንደገና ለግዳጅ በቃ::

ይህ ጀግና፤ ከሚያዝያ ወር 1970 ጀምሮ ኤርትራ ወደሚገኘው 2ኛው አየር ምድብ እንዲዛወር ተደረገ። በዛብህ ጴጥሮስ የሶማሊያን ወረራ ለመቀልበስ ከሐምሌ ወር 1969 እስከ የካቲት ወር 1970 በተደረገ የመከላከልም ሆነ የማጥቃት ውጊያ 191 ጊዜ ወደጠላት ወረዳ በርሯል። የጠላትን እግረኛ እና የሜካናይዝድ ጦር፤ ተዋጊ አውሮፕላንና የራዳር ጣቢያዎችን ደምስሷል:: በዚህ የላቀ እና ታላቅ ሀገራዊ ተጋድሎ ላበረከተው አስተዋፅኦ በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት መስከረም 3 ቀን 1972 ዓ.ም "የላቀ የጦር ሜዳ ጀብዱ ሜዳይ" ሸልሞታል::

በዛብህ ጴጥሮስ ህዳር 21 ቀን 1972 ዓ.ም ለንባብ በበቃው "ታጠቅ" ለተሰኘ የሠራዊቱ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር "... እኛ ብንሞት ሌላ ሰው ይተካናል፤ መተኪያ የሌላት ኢትዮጵያ ከሞተች ግን ተተኪው ትውልድ ስለሚሞት ዋጋ አይኖረውም:: የሀገርን ሉአላዊነት በአስተማማኝነት መጠበቅ ቆራጥነት እና ልበ ሙሉነት ይጠይቃል:: እኛ በሕይወት ቆመን እያየን ጠላት አንዲት ስንዝር መሬት ቆርሶ መሄድ ቀርቶ በአንድ እግሩ እንኳ ሊቆምባት አይችልም:: ከሀገር ወዲያ ሌላ መኖሪያ ዋሻ ስለሌለ በሃገር እና በነፃነት ጉዳይ ምንም ቀልድ ሊኖር አይችልም::..."ነበር ያለው።

ከሶማሊያ ወረራ በኋላ ወደ ኤርትራ ዘምቶ እስከ 1977 ድረስ ግዳጁን በአግባቡ የተወጣው ኮሎኔል በዛብህ፤ በ1977 ዓ.ም (ከሻዕቢያ)ኤርትሪያ ጋር እየተዋጋ ሳለ አውሮፕላኑ ተመታ:: በዚህን ጊዜ ወደተነሳበት ቦታ አውሮፕላኑን መመለስ ያልቻለው በዛብህ በሻዕቢያ(ኤርትራ)እጅ ወደቀ:: በዚህ ምክንያት እስረኛ ሆኖ በ1983 ዓ.ም ከእስር ተለቆ ከቤተሰቡ ጋ መቀላቀልም ችሎ ነበር::

ከ7 ዓመት በኋላ በ1990ዓ.ም በኤርትራና ኢትዮጵያ መካከል በተነሳ ጦርነት ዳግም ለመሳተፍ በቃ::ግንቦት 5 ቀን 1990 ዓ.ም ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ወደ ኤርትራ ምድር ዘልቀው ከገቡ የኢትዮጵያ አየር ሃይል ተዋጊዎች አንዱ ነበር:: የሚያበረውን አውሮፕላን እጅግ ዝቅ አድርጎ ሲበር እንደገና በኤርትራ ኃይሎች እጅ ወደቀ ተማርኮም እስረኛ ሆነ:: ኮሎኔል በዛብህ ለረጅም ጊዜ በፖለቲካ ተሳትፏቸው የሚታወቁት የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ወንድም ነው። ኮሎኔል በዛብህ በውጊያ ወቅት በኤርትራ ኃይሎች ከተያዘ በኋላ በህይወት አለ ወይስ የለም የሚል ድምዳሜ ላይ እስካሁን አለመደረሱን ቤተሰቦቻቸው ይገልፃሉ።

በጉዳዩ ላይ በተደጋጋሚ አስተያየት የሚሠጡት አንጋፋው ፖለቲከኛ በየነ ጴጥሮስ ወንድማቸው "በዛብህ በህይወት ላለመኖሩ በቂ ማስረጃ" አለመገኘቱን ይገልፃሉ። በህይወት አለ የሚሉ መኖራቸውን የሚያነሱት ፕሮፌሰር በየነ፤ አሁን ይህንን ማረጋገጥ ያለበት የኤርትራ መንግሥት መሆኑን ያነሳሉ።

አሁን ላይ ሞቷል እያሉ የሚጽፉት ነገር የዐይን እማኞች ከሚሉት ጋር እንደሚጋጭም ነው የሚያረጋግጡት። የኮሎኔል በዛብህን ጉዳይ በተመለከተ ማረጋገጥ ያለበት የኤርትራ መንግሥት ነው ቢሉም በየደረጃው ያሉ የኤርትራ ባለሥልጣናት ግን በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ነበር።

ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሠራዊት አባል ሆኖ በተሰማራባቸው አውደ ውጊያ ግንባሮች ከፍተኛ ጀብድ እየፈፀመ የኖረ የሀገር ኩራት የሆነ ጀግና ነው። ጀግናው ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ከወይዘሮ ወይንሸት ኃይሌ ጋር ትዳር መሥርተው ሶስት ወንድና ሁለት ሴት በድምሩ አምስት ልጆችን አፍርተዋል::

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
አል-ዓለም
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የሸገር አትሌቲክስ ክለብን ጠንካራ ተፎካካሪ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው

**ዓለማየሁ ግዛው**

የሸገር ከተማ ስፖርት ክለብ ከተቋቋመ ጥቂት ጊዜን ብቻ ነው የተቆጠረው፡፡ ክለቡ የተዋቀረው በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ካሉት አምስት ከተሞች የተውጣጡ የተለያዩ ክለቦችን በመያዝ ሲሆን እግር ኳስ፣ ቅርጫት ኳስን እና አትሌቲክስን አቅፎ ወደ እንቅስቃሴ መግባቱ ይታወቃል፡፡ ክለቡ በነዚህ ስፖርቶች ተሳትፎውን የጀመረ ሲሆን አትሌቲክሱም በቅርቡ እንቅስቃሴውን የተቀላቀለ ስፖርት ነው፡፡

ክለቡ በአትሌቲክስ ስፖርት ተፎካካሪና አሉ ከሚባሉ የአገሪቱ የአትሌቲክስ ክለቦች አንዱ የመሆን ተስፋን ሰንቋል። ከተቋቋመ 2 ወራትን ብቻ ያስቆጠረ ሲሆን እስካሁን ያደረጋቸው ውድድሮችም በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት 198 አትሌቶችን በመያዝ ወደ ሥልጠና የገባ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 60 አትሌቶችን ይዞ ጉዞውን ቀጥሏል። በቀጣይ የቡድኑን አትሌቶች ቁጥር በመጨመር እስከ 120 በማድረስ ጠንካራ ተፎካካሪና ተፅዕኖ ፈጣሪ የአትሌቲክስ ክለብ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ተገልጿል። በዚህም ከአገር አቀፍ ደረጃ አልፎ በዓለም ኢትዮጵያን በመወከል ውጤት የሚያስመዘግቡ አትሌቶችን ለማፍራት አስፈላጊው ዝግጅት እንደተደረገ ተጠቁሟል።

ክለቡ ከተመሠረተበት ወቅት ጀምሮ ዝግጅቱን በአግባቡ እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን፣ በ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ለመሳተፍ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ እንደሆነና ተፎካካሪና ውጤታማ ለመሆንም አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ የክለቡ ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌቱ ሽፈራው ገልጸዋል፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሰሞኑን ባዘጋጀው የአጭር፣ መካከለኛ፣ 3 ሺ ሜትር መሰናክል፣ የሜዳ ተግባራትና ርምጃ ውድድር የአቋም መለኪያ ሻምፒዮና በመሳተፍ የክለቡን ወቅታዊ ብቃት ለክቷል፡፡ ክለቡ አዲስ እንደመሆኑ በተወሰኑ ስፖርት ዓይነቶች የተወሰኑ አትሌቶችን ይዞ የቀረበ ሲሆን 35 አትሌቶችን አሳትፎ፣ በውድድሩ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ማሳየት ችሏል፡፡ ከወራት በፊት መቐለ በተካሄደው የሪሌይ ውድድርም የመጀመሪያ የነጥብ ተሳትፎውን አድርጎ ስድስተኛ ደረጃን ይዞ ፈጽሟል፡፡



**የሸገር ከተማ አትሌቲክስ ክለብ 60 አትሌቶችን አቅፎ በቅርቡ አገር አቀፍ ውድድሮች ላይ እየተሳተፈ ነው፣**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያዘጋጀው የአቋም መለኪያ ውድድር ክለቡ አቋሙን እንዲመለከትና ያለበትን ደረጃ አውቆ ከሌሎች ቡድኖች ጋር ለመፎካከር የሚያስችለውን ዕድል ለመፍጠር እንደሚረዳው አቶ ጌቱ ሽፈራው ተናግረዋል፡፡ ክለቡ አዲስ እንደመሆኑ በቀጣይ ምን መሥራት እንዳለበት፣ ጉድለቱን ለመለየትና አስተካክሎ ለኢትዮጵያ ሻምፒዮና እንዲሁም ለሌሎች ውድድሮች ጥሩ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ እንደሚያግዝ ገልፀዋል፡፡

ክለቡን ውጤታማና ተፎካካሪ ለማድረግ አመራሩ ቁርጠኛ እንደሆነና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለሟሟላት በጀት መመደቡን ሥራ አስኪያጁ ጠቁመዋል፡፡ በዚህም በግብዓት በኩል እስከ አሁን ችግር እንደሌለና ወደ ፊትም ይኖራል ተብሎ እንደማይታሰብ አክለውም፣ ክለቡ አሁን ያሳየውን ብቃት አጠናክሮ ከሠራ ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣም ያላቸውን እምነት ተናግረዋል፡፡

ክለቡ ለሚፈልገው ውጤታማነት መስፈርቶችን አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ ብቃትን ብቻ መሠረት በማድረግ ከሁሉም ክልሎች ሁሉንም መስፈርት ያማከለ የአትሌቶች ምርጫ በማድረግ ራሱን አጠናክሮ በአጭር ጊዜ ተፎካካሪ ከሆኑት የሀገሪቱ ክለቦች አንዱ የመሆን ዕቅድ አለው፡፡ ለዚህም ሁሉን አካታች፣ ውጤታማና ለሀገር የሚጠቅም ዓላማን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ከተመሠረቱ ረጅም ዓመታትን ካስቆጠሩ፣ ልምድ ካላቸውና ጠንካራ ክለቦች ጋር ለመፎካከር ከተማው አካባቢ የሚገኙትን አትሌቶች አሰባስቦ ወደ ክለቡ መቀላቀልና ተተኪ አትሌቶችን ማፍራትንም አቅዶ እየሠራ ነው፡፡ በዚህም ከፕሮጀክቶች ከአካዳሚና ከሌሎች ቦታዎች አትሌቶችን በማሳደግ እራሱን የማጠናከርና ተፎካካሪ የማድረግ ሥራን ያከናውናል፡፡ «ተፎካካሪና ተፅዕኖ የሚፈጥር አትሌቲክስ ክለብ የማይሆንበት ምክንያት የለም፣ በአቋም መለኪያ ውድድርም ተፎካካሪ መሆኑን አሳይቷል» ያሉት ሥራ አስኪያጁ፣ ክለቡ በኦሮሚያ ክልል የተዘጋጁ ውድድሮች ላይ 30 አትሌቶችን ይዞ እንደተሳተፈ በማስታወስ በትንሽ አትሌቶች ተፎካካሪ በመሆን ሁለተኛ ደረጃን ይዞ እንዳጠናቀቀ ይናገራሉ፡፡

ክለቡ የቀጠራቸውና ቅጥር ሂደት ላይ ያሉት አሠልጣኞች ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ማስጠራት የቻሉ ውጤታማና ብቃት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም አትሌቶችን ለመሳብና ውጤታማ ክለብን ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት አስተዋፅዖው የጎላ እንደሚሆን ሥራ አስኪያጁ ያምናሉ፡፡ በዚህም ክለቡ ማስታወቂያ አውጥቶ ከሀገሪቱ አሉ የተባሉትን አሠልጣኞች አወዳድሮ መቅጠሩንና የላቀ ብቃት ያለው የአሠልጣኞች ስብስብ መፍጠሩን አስረድተዋል፡፡

የክለቡ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አከፋፈል ብቃትን ብቻ መሠረት ያደረገና አትሌቶች በተሳተፉበት ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ውድድሮች ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ነው፡፡በዚህም መሠረት ኦሊምፒክ የተሳተፈ አትሌት መነሻ ክፍያ ከፍ የሚል ሲሆን ሌሎች አትሌቶችን ለመሳብ እንደ ጉርሻ ሊሆን እንደሚችልም ተጠቅሷል፡፡